

የድርጅቱ መሥራቾች ከፊል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት በ፲፱፻፶፭ ዓ. ም. የተ
መሠረተበትን ፳ኛ ዓመት በ፲፱፻፸፭ ዓ. ም. ሲያከብር የወጣ ልዩ ዕትም ።



ድርጅቱ በተቋቋመ ጊዜ ሥራውን የጀመረበት ጽ/ ቤት ፤

ዋጋው ሃምሳ ሣንቲም ቁጥር ፫ መስከረም ፲፱፻፸፭ ዓ.ም.

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፤ ሥርዓትና ዜና ፤ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ። »


አዘጋጅ
ራደ አስረስ ፤

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ሐዋርያዊ ድርጅት
የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ
በወር አንድ ጊዜ
እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 116616
የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፤


## የ፲፱፻፸፭ ዓ· ም· በዓላትና አጽዋማት ፤

| | | |
|---|---|---|
| አበቅቴ . . . | | ፲፯ |
| መጥቅዕ . . . | | ፲፫ |
| ነነዌ የካቲት . . | ፳፩ | ቀን |
| ዐቢይ ጾም መጋቢት | ፭ | » |
| ደብረ ዘይት ሚያዝያ | ፱ | » |
| ሆሣዕና ሚያዝያ | ፳፫ | » |
| ስቅለት » | ፳፰ | » |
| ትንሣኤ » | ፴ | » |
| ርክበ ካህናት ግንቦት | ፳፬ | » |
| ዕርገት . . . . ሰኔ | ፱ | » |
| ጰራቅሊጦስ . . . » | ፲፱ | » |
| ጾመ ሐዋርያት » | ፳ | » |
| ጾመ ድኅነት » | ፳፪ | » |

## ማ ው ጫ

**አርእስት ፤** — **ገጽ**


የሃያ ዓመት ሐዋርያዊ ጉዞ . . . . . . . . . . ፫
የቅዱስ ፓትርያርኩ ፯ኛ ዓመት በዓለ ሢመት . . . ፭
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት የሃያ ዓመት የሥራ ርምጃ . . . . . . . . . . ፯
የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ንግግር . . ፰
« ሒዱና አስተምሩ » . . . . . . . . . . . . ፲
በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መድረክ የሥነ ጽሑፍ ታሪክ ፲፭
አዲስ ዓመት . . . . . . . . . . . . . ፳፩
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያ ሐዋርያት ፳፫
የሰንበት ትምህርት ቤት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን . . . . . . . . . . . ፳፱
ወላድ ሴት . . . . . . . . . . . . . . ፴፩




ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ፤

www.ethiopianorthodox.org

( ርእሰ አንቀጽ )

# የሐያ ዓመት ሐዋርያዊ ጉዞ

« እስኩ ጸውዓ ለዕለት እንተ ትማልም ኃለፈት እስኪ ያለፈችውን የትናንትዋን ቀን ጥራት » በማለት ዕዝራ ሱቱኤል እንደተናገረው ሁሉ ጊዜ እንደወራጅ ውሃ ነው ፤ ወራጅ ወንዝ ተገድቦ የሚወርደውን ውሃ እግረ መንገዱን ለመስኖ ወይም ለመጠጥ አገልግሎት ካላዋሉት በቀር አልፎ ከሜሄድ አይገታም ። ጊዜም እንደዚሁ በፈጣን ውድድርና እሽቅድምድም እየሠሩ ካላሣለፉት አልፎ ከሄደ በኋላ መለስ ብሎ የሚያይበት አንገት የለውም ።

ጊዜ ወይም ዕድሜ ከእግዚአብሔር በአደራ መልክ የተሰጠ በረከት ነው ፤ ብልሆች ወጥተው ወርደው ያተርፉበታል ። ሰነፎች ግን ምንም ሳይጠቀሙበት እንደጨርቅ ያልቃል ። አንድ ደራሲ ሲናገር « መላእክት በሚመቸን የወርቅ አልጋ ላይ አስተኝተውም ሆነ አስቀምጠው ወደሰማይ እንዲወስዱን አምላክ ተስፋ አልሰጠም » ይልነበር ። የተፈጠርነው ለሥራ ነው ማለቱ ነው ። ፈላስፋው ቦልቴር ሥራ ያበዛ ስለነበር አንድ የሕክምና አማካሪ ዕረፍት ያደርግ ዘንድ ቢጠይቀው « የተፈጠርነው ለሥራ ብቻ ነው ፤ ዕረፍቱንማ ወደን እስክንጠላ በመቃብር ዓለም እንጠግበዋለን » አለ ይባላል ። ቅዱስ አውግስጢኖስ የተባለ የሰሜን አፍሪቃዊት አገር ሊቅ « ሥራ ራሱ ጸሎት ነው » ማለቱ ይታወሳል ። ሰሎሞንምበምሳሌው የሚሠራ ሰው በሚያርፍበት ጊዜ እንኳ ጣፋጭ እንቅልፍን ያገኛል ሲል ጽፎአል ።

እንግዲያውስ አለመሥራት በአንድ በኩልኃጢአት በሌላም በኩል የጤና ጠንቅ መሆኑ መታወቅ አለበት ። « መሬት ሁሉን ነገር ተሸክማ ስትኖር ፤ የሚከብዳት የለም ከሰነፍ ሰው በቀር « አለ ባለቅኔው ። ይህም ሁሉ ሆኖ የጊዜን ወርቅነት የሥራን ክቡርነት የተረዱ ጤናማ ሰዎች ምንጊዜም በቁጥር ያነሱ ናቸው ። ጊዜ ካለፈ በኋላ መንቃት ባቡር ከተነሣ ወይም ገበያ ከተበተነ በኋላ እንደ መድረስ ይቆጠራል ።

በመሠረቱ « የወጡ መጣፈጥ ከድስቱ ትልቅነት አይደለም » እንዲሉ ብዙ ሥራ ለመሥራት የሚያስችል የዘመን ብዛት ወይም የዕድሜ መርዘም ጉዳይ ሊሆን አይችልም ። ምንም ነገር ሳይሠራበት የሚያልፍ ረጅም ዘመንና ብዙ ሥራ ሠርተው የሚጠቀሙበትም አጭር ጊዜ የመኖር አጋጣሚም አለና ነው ። ለማስረጃ ያህል ታላቁ ናፖሊዮን በ፲፰ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለሀገሩ የሠራው ቁም ነገር ወይም ዕድገት ሁሉ ሲመዛዘን ከርሱ በፊት የነበሩ መሪዎች ( ነገሥታት ) በ፫፻ ዓመት ጊዜ ውስጥ ከሠሩት ይበልጣል የሚል ታሪካዊ አነጋገርአለ ። « በትንሽ ማረሻ ትልቅ እርሻ » እንዲሉ ።

እነሆ ይህም ወቅት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት የተመሠረተበትን ፳ኛ ዓመት የሚያከብርበት ጊዜ ነው ። ታዲያ ፳ ዓመት የአንድ መካከለኛ አዳጊ ወጣት ዕድሜ መሆኑ ነው እንበል ። ድርጅቱም ከተመሠረተበት ጊዜ አንሥቶ እስካሁን ያለው ዘመን ሲታሰብ ገና አዳጊ ድርጅት ነው ማለት ይቻላል ። ነገር ግን በመንፈሳዊ ሥራዎች የብዙ መቶና ሺህ ዓመት ዕድሜ ካላቸውመን ፈሳዊውያን ድርጅቶች ጋር የሚወዳደር ሆኖ ተገኝቶአል ። ይህንም ለማለት የሚያስችሉ ብዙ ምክንያቶች መኖራቸውን በዚሁ እትም ላይ በቀረበው የ፳ ዓመት አጭር ሪፖርት መመልከት ይቻላል ።

ይህም ሁሉ ሆኖ የድርጅቱ የሥራ እርምጃ ግሥጋሜና ዕድገቱ በዚህ ብቻ ይገታል ማለት አይደለም ። ገናእጅግ ብዙ የሆኑ የሥራ ዕቅዶች ይጠብቁ ታል ። ከተግባሩም ማየት እንደሚቻል ድርጅቱ ለቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎት ሰጪ ብቻም አይደለም ። ከመንፈሳዊ አገልግሎቱ ጋር ሀገርንና ሕዝብን የሚጠቅሙ የማኅበራዊ ኑሮ ነክ የባህልንና የታሪክ የሥነ ጽሑፍና የትምህርት ዕድገትን የሚመለከት ግልጋሎት ሲያበረክት የኖረና የሚቀጥልም ነው ።

ይህም ለመሆን የቻለው በእግዚአብሔር ፈቃድ ተጠርተው በክርስቶስ ፍቅር የታነጸ ሕይወት ያላቸው በትእዛዝ ሳይሆን በፍጹም ፈቃደኛነት ኃላፊነታቸውን ተገንዝበው ፍቅርና ሰላም በሰፈነበት



www.ethiopianorthodox.org

ጠንካራ ሥነ ሥርዓት በመግባባትና በመተሳሰብ ሠርተው የሚያሠሩ ኃላፊዎችም ፤ ሠራተኞችም በመ
ኖራቸው ነው ። የእግዚአብሔርም ቅዱስ መንፈስ እንዳልተለየው የሚያስረዳው ድርጅቱ ከተመሠረተ
በት ጊዜ አንሥቶ በሥራ ክቡርነት የሚያምኑ አሠሪዎችንና ሠራተኞችን ያጣበት ጊዜ አለመኖሩ ነው ።

በዚህም ሁሉ ሒደት ድርጅቱ በብሔር አቀፍ ደረጃ የታወቀ ከመሆኑ የተነሣ ያለውን ዕቅድ
ሁሉ በተግባር ለመተርጐም አጋጣሚው ችግር ወንጌልን የሚሰብኩ የበቁ መምህራን በቁጥር ማነስ ብቻ
ነው ። በመሠረቱም የወንጌል ስብከት ሥራ እንደማንኛውም ተግባር ሁሉ ዕለቱን ተጠንቶ ዕለቱን
በሥራ ላይ የሚውል ነገር አይደለም ። ከበቂ ትምህርት ጋር የረጅም ጊዜ ልምድና ለእግዚአብሔር
ሥራ ራስን አሳልፎ የመስጠትን ፍጹም ፈቃደኛነት ይጠይቃል ። ለምሳሌ ክርስቶስ ራሱ እንኳን ፲፪ቱን
ሐዋርያትና ፸፪ቱን አርድዕት በወንጌል ስብከት ሥራ ላይ ያሠማራቸው ቦዘኔዎችን ከየሜዳው በመሰ
ብሰብ ሳይሆን ከየምድብ ሥራቸው ላይ መርጦ በመጥራት ፫ ዓመት ከ፫ ወር ካሠለጠነ በኋላ በመንፈስ
ቅዱስ ቃኝቶ በማዘጋጀት ነው ። ቀድሞውኑም ቢሆን አብዛኞቹ ምሁራን እሪት እንደነበሩ ከተግባራ
ቸው ይታያል ።

በተለይም በአሁኑ ጊዜ የወንጌል ስብከት መምህራን አሠራር ብርቱ ጥንቃቄን ፈሊጥንና የረ
ቀቀ መንፈሳዊ ጥበብን የሚጠይቅ ዝግጅት የሚያስፈልገው ጉዳይ ነው ። ለዚህም ወሳኙ ቁም ነገር
ከመጻሕፍተ ብሉያትና ሐዲሳት ትርጉም ጋር የሊቃውንትና የመጽሐፈ መነኰሳትን ፤ የሕግጋትን ትርጉም
ጥናት ጭምር ይጠይቃል ። ይህም ብቻ ሳይሆን ፤ ከሌሎች አገሮችም የላቀ ልምድ ለመቅሰም የሚያ
ስችሉ መጻሕፍትን አንብቦ ለመተርጐም ከዓለም አቀፍ ቋንቋዎች አንድም ሆነ ሁለት ያህል አውቆ
ለመገኘት ዘመናዊ ትምህርት በብርቱ አስፈላጊ ነው ። ከዚህ ውጭ ያለው የይድረስ ይድረስ አሠራር
ግን ለወንጌል ስብከት ሥራ በቂ ማድረግ አይችልም ። ለዚህም ሁሉ ለወንጌል ሰባክያን የሥራ ክንውን
የመንፈስ ቅዱስ ረዳትነት እጅግ አስፈላጊ ነው ።

ስለዚህ ይህን የድርጅቱን የ፳ ዓመት ሐዋርያዊ ጉዞ የሥራ ውጤት የተመለከቱ የኦርቶዶክ
ሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባሎችና ወዳጆች ሁሉ ወደፊት ከዚህ የላቀ እርምጃ እንዲኖረው ለድ
ርጅቱ የሚሰጡት የሀሳብና የተግባር ርዳታም ቢሆን ካለፈው የበለጠ እንደሚሆን በተስፋ ይጠበቃል ።
ባለፈው ስላደረጉትም ርዳታ ሁሉ እግዚአብሔር ዋጋቸውን እንዲከፍላቸው የድርጅቱ ሠራተኞ
ሁሉ የዘወትር ጸሎት ነው ።



# የቅዱስ ፓትርያርኩ ፲፪ኛ ዓመት በዓለ ሢመት
# በ ደ ማ ቅ ሁ ኔ ታ ተ ከ በ ረ

የሦስተኛው ፓትርያርክ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክና የቅዱስ ሲኖዶስ ሊቀ መንበር ፲፪ኛ ዓመት በዓለ ሢመት መታሰቢያ ነሐሴ ፳፫ ቀን ፲፱፻ ፹፬ ዓ.ም. እጅግ ደማቅ በሆነ ሥነ ሥርዓት ተከብሮ ውሎአል ።

በዚሁ በዓል ላይ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ከአዲስ አበባ ከተማ አጠቃላይ ምክር ቤት የተወከሉ ባለሥልጣን ፣ የልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ፣ የአድባራትና ገዳማት አስተዳዳሪዎች ፣ የሰበካ ጉባኤ ምክትል ሊቃነ መናብርት ከአዲስ አበባ አድባራትና ገዳማት የተውጣጡ ልብሰ ተክህኖ የለበሱ ካህናትና መዘምራን ከአዲስ አበባ አድባራት የሰንበት ት/ቤት የተውጣጡ ወጣት መዘምራን በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ምዕመናን ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሐዋርያዊ ድርጅት ባለሥልጣኖችና ሠራተኞች የጠቅላይ ቤተ ክህነት የመምሪያ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ተገኝተዋል።

በዕለቱ በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም በቅዱስነታቸው መሪነት ሥርዓተ ቅዳሴው ተከናውኖ እንደተፈጸመና ቅዱስነታቸው ከተዘጋጀላቸው የክብርቦታ እንደደረሱ ለበዓሉ የተዘጋጀው ግስ በተመረጡ ሊቃውንት ተቃኝቶ እንዳበቃ ጥንግ ድርብ የለበሱ መዘምራን ፣ እንዲሁም የተሰበሰቡት ሊቃውንት ለ፳ ደቂቃ ያህል አሸብሺበውታል ። ከዚያም የተለያዩ ሊቃውንት ቅኔ ያበረከቱ ሲሆን ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው በዓሉን ንና የቤተ ክርስቲያንን ህላዌ የሚገልጽ እጅግ ጠቃሚ የሆነ ንግግር አድርገዋል ።

በመጨረሻም ቅዱስነታቸው አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያንን ሂደትና የሃይማኖትን ፅንዓት የሚመለከት ጠቃሚ የሆነ ቃለ ምዕዳን አስተላልፈዋል

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በዕለቱ ያስተላለፉት ቃለ ምዕዳን ሙሉ ቃል የሚከተለው ነው ።

<u>በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ፤</u>

የተወደዳችሁ ካህናትና ምእመናን የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምና ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን ።

ነቢዩ ዳዊት «አንተ ፈጠርከ ፀሐየ ወወርኃ ወአንተ ገበርከ አድባረ ምድር ኵሎ ክረምተ ወሐጋየ ዘአንተ ፈጠርከ ወተዘከር ዘንተ ተግባረከ አንተ ፀሐይንና ጨረቃን ፈጠርክ ፣ የምድርን ዳርቻም አደረግህ ፤ ክረምትና በጋን አዘጋጀህ፣ይህን ፍጥረትህን አስብ» ሲል በእግዚአብሔር ፊት እንደዘመረ ተጽፎአል ። መዝሙር ፸፫ ቁጥር ፲፮ እስከ ፲፯

ይህ ቃል በአንድ በኩል ይህ ዓለም በጥንተ ተፈጥሮ የእግዚአብሔር ዕጹብ ድንቅ ሥራ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የዓለም ፈጣሪ ፍጥረቱን እንዲያስብ በጸሎት በመጠየቅ የዓለምን ደህንነት በረድኤተ እግዚአብሔር ማስጠበቅ ምንጊዜም የቤተ እግዚአብሔር መጋቢዎች ከሚሠየሙበት ከፍተኛ መንፈሳዊ ተልእኮ አንዱና ዋናው ክፍል መሆኑን በግልጽ ያመለክታል ። «አንተ ሁሉን ፈጠርክ ከአለ በኋላ ይህን ፍጥረትህን አስብ» በማለት ነቢዩ በነቢይነቱ የፈጸመው ይህ የዓለም መምህርነትና የመጋቢነት ተልእኮ በየጊዜው በዚህ ዓለም ላይ ከሚነሱ መንፈሳውያን መጋቢዎች ሁሉ ለሚጠበቀው መንፈሳዊ ተልእኮ አፈጻጸም መልካም ምሳሌነት ያለው ትምህርታዊ ኃይለ ቃል ነው ። በእርግጥ እግዚአብሔር ለፍጥረቱ ሁሉ የሚያስብ የዓለም ሠራዒ መጋቢ እንደ ሆነ ለተገልጋዩ ሕዝብ በብዙ መንገድ ገልጾአል ።

ይኸውም አንደኛው በመንፈስ እግዚአብሔር እየተቃኘ የሚናገረው የሰው አንደበት ሲሆን ሌላው ደግሞ በየጊዜው የሚፈጸመው አስደናቂ ሥራው ነው ።

ሁላችንም እንደምናውቀው አሁን ያለነው እግዚአብሔር ለፍጥረቱ በማሰብ ምድርን በዝናመ ምሕረት በጠለ በረከት በሚጎበኝበትና የፈጣሪነቱንም ኃይል ለፍጥረቱ በተግባር በሚገለጽበት በተለይ ለኛ ባዘጋጀው የክረምት ወራት ነው ።

ይህ ወቅት የሥነ ፍጥረት ጌታ እግዚአብሔር በጥንተ ተፈጥሮ «ምድር ሁሉን ታብቅል » ሲል የተናገረው አምላካዊ ቃል በትክክል በተግባር ሲተረጐም የሚታይበትና በርግጥ ለፍጥረቱ የቱን ያህል እንደሚያስብ የቸርነቱ ምሥጢር በምድር ላይ በይበልጥ ጐልቶ የሚታወቅበት የሥነ ፍጥረት ወርቃማ ጊዜ ስለሆነ የእግዚአብሔርን ሠራዒ መጋቢነት በአምላካዊ ግብሩ ለማረጋገጥ ከዚህ የተሻለ ትምህርታዊ ወቅት የለም ።

እግዚአብሔር አምላክ የፈጣሪነቱንና የመጋቢነቱን ኃይል ከገለጸባቸው ፍጥረታት ሁሉ ተመሳሳይና ተወዳዳሪ የሌለው ታላቅ ፍጡር የሰው ልጅ ብቻ ስለሆነ የሰው ሕይወት ከማንኛውም ሕይወት ሁሉ ይበልጣል ።



www.ethiopianorthodox.org

ለሕይወት አስፈላጊ የሆነው ነገር ሁሉ እንዲህ በምድር ላይ ተሟልቶና ተትረፍርፎ ሊገኝ የቻለውም ምድር የሰው ልጅ መኖሪያ በመሆኗ ነው ።

እግዚአብሔር ለፍጥረቱ በማሰብ በአርአያውና በአምሳሉ ለፈጠረው የሰው ልጅ በረከተ ሥጋና በረከተ ነፍ ስን የምታስጥ በልጁ ክቡር ደም የተ ዋጀች አንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲ ያንን በምድር ላይ መሥርቷል ። ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ የተመሠረተ ችው ሰላምንና ፍቅርን ነፃነትንና እኩ ልነትን ፡ ፍትሕና እውነተኛ ፍቅርን ለዓለም በመስበክና በማስተማር የሰ ውን ዘር ሁሉ ለሰማያዊና ምድራዊ በረከት ለማዘጋጀት ሲሆን ይህን ከፍ ተኛ ተልእኮ በትክክል ለመፈጸም የም ንችለውም እግዚአብሔር ምንጊዜም ሰውን በቸርነቱ እንደሚያስብ ሁሉ የሰውም ልጅ እንዲሁ ምን ጊዜም እግዚአብሔርን እንዲያስብ በማድ ረግ ነው ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲ ያን በዓለም ላይ የብዙዎች ጥንታው ያን አብያተ ክርስቲያናት በኩር እንደ መሆንዋ መጠን በቅዱስ ተልእኮ የረ ጅም ጊዜ ታሪክ አላት ወንጌላዊው ዮሐንስ በቅዱስ ብሥራቱ እንደተናገ ረው እግዚአብሔር አንድ ልጁን ለሞት አሳልፎ እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን ወዶ አል ፤ ዮሐንስ ፫–፲፮ ፤ በቅዱስ ደሙ ዓለ ምን በመዋጀት እግዚአብሔር ለዓለም ያለውን ጽኑዕ ፍቅር የገለጸበት ይህ አንድ ልጁም የሐዲስ ኪዳን ቤተ ክር ስቲያን ርእስና መሠረት የሆነው ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ።

የእግዚአብሔር ልጅ ጌታችን ኢየ ሱስ ክርስቶስ እስከ ሞት ድረስ የወ ደደውን ዓለም እስከ መጨረሻ በመ ውደድ ከእርሱ በኋላም የእርሱን አር አያ በመከተል የዓለም ብርሃንና የም ድር ጨው ሆነው የሚያገለግሉ መን ፈሳውያን መጋቢዎችን ተክቷል ፤ምን ጊዜም ይተካል ።

እኛ ሁላችንም በአሁኑ ወቅት ለዚህ ከፍተኛ ተልእኮ የተጠራን ልዑካን ስለ ሆን ነቢዩ እንደተናገረው በመንፈሳዊ ተልእኮአችን እግዚአብሔር ሰውን በቸርነቱ እንዲያስበው ሰውም እግ ዚአብሔርን እንዲያመሰግን በማድ ረግ በእርግጥ የዓለም ብርሃንና የም ድር ጨው ሆነን መገኘት ይኖርብናል

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ይህን ከፍተኛ ኃላፊነት በትክክል መወጣት እንደአለባት በበለጠ በመገንዘብ በአ ሁኑ ጊዜ በአምስት ቦታዎች የካህና ናት ፤ ማሰልጠኛ ጣቢያዎችን በማቋ ቋም ያሥራ አራቱን ክፍላተ ሀገር ካህ ናት በየተራ በማሰልጠን ላይ ትገኛለች የአዲስ አበባ ከተማም እንዲሁ እንደ አንድ ክፍለ ሀገር ስለሚቆጠር ለካ ህናቱ ተመሳሳይ የማሰልጠኛ ትምህ ርት እንዲሰጥ ተወስኖ ትምህርቱ በአ ሁኑ ጊዜ በጠቅላይ ቤተ ክህነት አዳ ራሽ በመሰጠት ላይ ይገኛል

በሌላም በኩል የቤተ ክርስቲያኒቱ ካህናትና ምእመናን በአሁኑ ጊዜ ከዳር እስከ ዳር በየአጥቢያው በሰበካ ጉባኤ በመደራጀት ድህነትንና የኑሮ ልዩነ ትን ከቤተ ክርስቲያን አካባቢ ለማስ ወገድ የሚያደርጉት የኅብረት ጥረት እጅግ በጣም የሚያስደስትና የሚያስ መካም ነው።

በውጭ ግንኙነትም በኩል የኢትዮ ጵያ ቤተ ክርስቲያን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ መሥራች አባል እንደመሆኗ መጠን በአሁኑ ጊዜ በዓ ለም አቀፍ ደረጃ በሚደረጉት ጉባኤ ያት ላይ በመልእክተኞቿ አማካይነት ሙሉ ተሳትፎ በማድረግ የዘር ልዩነ ትንና ጸረ ሰላም የሆነ አዝማሚያን ሁሉ በዓለም አቀፍ ደረጃ በመቃወምና እንዲሁም በአንፃሩ ለዓለም ሰላምና ፍትሕ ከቆሙ የሰላም ሰዎች ጋር በመ ቆም የምታበረክተው ዓለም አቀፍ ተልእኮ በቀላሉ የሚገመት አይደለም

ከዚህም በተጨማሪ ከውጪ የክር ስትና ዓለም ጋር የምታደርገው ዓለም አቀፍ ግንኙነት የልማት እቅዶችን ለመንደፍና ለማስፈጸም የሚያስችል የውጭ እርዳታና ትብብር ለማግኘትም ስላስቻላት በአሁኑ ጊዜ ኅብረተ ሰቡን የሚጠቅሙና የቤተ ክርስቲያን አገል ጋዮችንም ኑሮ ለማሻሻል የሚያስችሉ አያሌ የዕድገት ተግባሮች በመከናወን ላይ ናቸው ።

ወደፊትም ረሀብንና በሽታን እንዲ ሁም የእውቀትና የኑሮ ኋላ ቀርነትን ከሀገሪቱ ለማስወገድ በብሔራዊ ደረጃ የሚወጣውን መመሪያ ሁሉ በመደ ገፍ የሚፈለግባትን ድርሻ ሁሉ ለመፈ ጸም ወደኋላ አትልም ፤ ይኸውም ምን ጊዜም ለሰው ልጅ ደኅንነት የሚደረግ ሥራ ሁሉ የእግዚአብሔር ፈቃድ ፈጻሚ በመሆኑ ነው ፤ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ያላደረገው መልካም ነገር የለም ፤ ቤተ ክርስቲያንም የሱን ፈለግ መከተል ግዴታዋ ስለሆነ በቃል ብቻ ሳይሆን በግብር ክርስቶስን ለመከተል ማንኛውም መልካም ነገር ሁሉ ለሰው ልጅ እንዲሆን ትጥራለች ።

እግዚአብሔር ሰውን እንደሚያስብ ሰውም እግዚአብሔርን በማሰብ የበ ረከተ ሰማይና በረከተ ምድር ባለቤት ይሆን ዘንድም የሚፈለገውን መንፈ ሳዊ አገልግሎት ሁሉ ትፈጽማለች

የዓለማት ፈጣሪ የሰማዩን ዝናምና የምድርን ፍሬ ያስምርልን ፤ ለዓለም ሰላምን ይስጥልን ፤

የሀገራችንን አንድነትና ሰላም ለማ ስከበር በየጠረፉ ብሔራዊ ግዳጃቸው ን በመፈጸም ላይ ለሚገኙ የኢትዮ ጵያ አርበኞች ሀብተ መዊዕን ይስጥ ልን ።

ሀገራችን ኢትዮጵያን በአንድነትና በነፃነት ለዘለዓለም ይባርክ ።



# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት

## የሐያ ዓመት የሥራ ርምጃ

ይህ ድርጅት በከተማም ሆነ በገ ጠረ ኢትዮጵያ ወደሚገኙ የኦርቶዶ ክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት የወንጌል መምህራንን እየላከ የወንጌ ልን ቃል ለማዳረስ ፤ ክርስትናን ለማ ስፋፋትና ክርስቲያኖች የተስተካከለ መንፈሳዊና ሥጋዊ ሕይወት እንዲኖ ራቸው ለማስተማር የተቋቋመ የኢት ዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክር ስቲያን ድርጅት ነው ።

ድርጅቱ በተለይ በአሁኑ ጊዜ ሥራ ውን የሚያካሒድባቸውና ከምእመ ናን ጋር ግንኙነት የሚያደርግባቸው ሀ— ድምፀ ተዋሕዶ ጋዜጣ ፤ ለ— ትንሣኤ መጽሔት ፤ ሐ—የሥነ ምግ ባር ተዘዋዋሪ ቡድን ናቸው ። በእነ ዚህ የትምህርት ማሰራጫ ዘዴዎች አማካይነት ከወንጌል ትምህርት ጋር ስለጤና ፤ ስለልማትና ስለማኅበራዊ ኑሮም ጭምር ያስተምራል ።

ሐዋርያዊ ድርጅት መቼና የት ተቋቋመ ?

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት በ፲፱፻፶፰ ዓ· ም· በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴ ድራል አቅራቢያ ሆኖ ከካቴድራሉ ንብረት ለቢሮ የሚሆን ራሱን የቻለ አንድ ቤት እንዲሰጠው ታዝዞ በት እዛዙ መሠረት ቤቱ ተሰጥቶት ተቋ ቋመ ።

ሐዋርያዊ ድርጅት እንዴት ተቋቋመ ?

ከላይ በተገለጸው መሠረት የአንድ ጠንካራ ድርጅት መቋቋም አስፈላጊ ከሆነ ዘንድ ይህ ድርጅት ራሱን ችሎ በቦርድ እንዲሠራ «የኢትዮጵያ ኦር ቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊ ድርጅት» በሚል ሥያሜ ተቋቋመ ።

ከዚያም ቀደም ሲል የድርጅቱን መቋቋም አስፈላጊነትና የሚያስፈል ጉትንም ነገሮች አጥንቶ እንዲያቀርብ ተቋቁሞ የነበረው ኮሚቴ ያቀረበውን ሐሳብ መንግሥት በቁጥር ፪ሺ፬፻፳/ ፳፫/፶፮ ሐምሌ ፲ ቀን ፲፱፻፶፰ ዓ.ም. በተጻፈ ትእዛዝ የቀረበውን ሐሳብ አጸደቀ ። በዚህም መሠረት ድርጅቱ በቦርድ እንዲመራ ሲደረግ የቦርዱም ሊቀ መንበር የመንበረ ፀባዖት ቅድ ስት ሥላሴ ካቴድራል ሊቀ ሥልጣ ናት እንዲሆን ተወሰነ ። ድርጅቱ ለመ ጀመሪያ ጊዜ ሥራውን ሲቀጥል በአ ጥኚው ኮሚቴ ሐሳብ መሠረት የሚ ከተሉት የሰው ፤ የገንዘብና የዕቃ አስ ፈላጊነት ለመንግሥት ቀርቦ በቁጥር ፭ሺ፬፻፹፪/ ፪ሺ፬፻፴፭/ ፯ ሚያዝያ ፲ ቀን ፲፱፻፶፰ ዓ. ም. በተጻፈ ማዘዣ ተፈቀደ ።

ድርጅቱ ሲቋቋም ለጊዜው እንዲ ኖሩት የተደረጉ የሰው ኃይል ፤ ዕቃ ዎችና በጀት

፩—ለአንድ ሥራውን በቅርብ ለሚ ቆጣጠር (ሥራ አስኪያጅ)በወር ፪፻፶—ብር በዓመት ሦስት ሺ ብር

፪—ለአንድ ጸሐፊ(ታይፒስት) ፪፻፶ ብር

፫—ለሦስት ሰባኪያን ለእያንዳንዳ ቸው ፪፻ ብር

፬—ለአንድ ተላላኪ ፳፭ ብር

፭—ለሥራ ማስኬጃ ፪፻ ብር

፮—የሚነገሩትን መልእክታት በመ ጽሐፍ መልክ ለማሳተም ፶ ብር በድምሩ አሥራ ስድስት ሺ አም ስት መቶ ብር ሲፈቀድ ፤ አስ ፈላጊ ዕቃዎችን ገዝቶ ድርጅቱን ራሱን አስችሎ ለመሥራት ፤—

፩—ለአንድ ኩምቢ ቦልክስዋገን ሰር ቪስ መግዣ ፭ሺ፷፪ ብር

፪—ለአንድ ቴፕሪኮርደር ከነሙሉ መሣሪያው መግዣ ፮፪

፫—ለአንድ አማርኛ የጽሕፈት መ ኪና ፬፪

በድምሩ ፮ሺ፷፪

ብር ወጭ ሆኖ ከጠቅላይ ቤተ ክህነት እንዲሰጥ ስለተፈቀደ በዚሁ መሠ ረት ከላይ በተጠቀሰው በጀት በነሐሴ ወር ፲፱፻፶፰ ዓ· ም· ሥራውን ጀመረ።

ከአንድ ወር ዝግጅት በኋላ መስከ ረም ፩ ቀን ፲፱፻፶፯ ዓ· ም· «አዲስ ዘመን» በሚል ርእስ የድርጅቱ የመ ጀመሪያ ሥራ አስኪያጅና «ዳግማዊ ጳውሎስ» በሚል የቅጽል ስም በም እመናን ዘንድ ይጠሩ በነበሩት በመ ልአከ ሰላም ሳሙኤል ተረፈ በተዘ ጋጀ መልእክት ፕሮግራሙን ከፈተ።

በዚህም መሠረት ከመስከረም ፩ ቀን ፲፱፻፶፯ ዓ·ም·ጀምሮ በቀን የ፴ደቂ



የድርጅቱ የመጀመሪያው ሥራ አስኪያጅ መልአከ ሰላም ሳሙኤል ተረፈ እኚህ ነበሩ ፤

ቃዎች በሳምንት የ፫ ሰዓት ተኩል መልእክት በማስተላለፍ ላይ ሳለ ለስብከቱ ሥራ ተጨማሪ አዘጋጅ አስ ፈለገ ። ስለአስፈለገም የጥንቱ የጽሕ

ተከታዩ ወደ ገጽ ፱ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ንግግር

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትሪያርክ ዘኢትዮጵያ

ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት

በዓሉን ለማክበር የተሰበሰባችሁ እንግዶቻችን ፣ የአድባራትና ገዳማት አስተዳዳሪዎች ፣ ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶቻችን ፣

ከሁሉ በፊት ታላቁ ሐዋርያ «በምንም ሊታወቅ የማይቻል እግዚአብሔር በፍጥረቱ ይታወቃል» እንዳለው ፍጥረቱ የሆኑት ሐዋርያት እግዚአብሔርን እየሰበኩ በአሕዛብ ፣ በልዩ ልዩ ነገዶችም እንዲታወቅ እንዳደረጉት ሁሉ ይህ በእነርሱ ኡግር የተቋቋመው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሐዋርያዊ ድርጅትም ለእግዚአብሔር መንግሥት መስፋፋትና ለክርስትና እምነት ዕድገት ዓይነተኛ ጥረት ያደረገ የሐያ ዓመት ለግላጋ ወጣት ስለሆነ ይህ እንዲሆን ላደረገ እግዚአብሔር ክብርና ምስጋና ይድረሰው እላለሁ ።

ቸር አምላክ በቅዱስ ዳዊት አድሮ «ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር» ብሎ እንደተናገረው ሁሉ ሀገራችን ኢትዮጵያ እግዚአብሔርን ሳታውቅ የኖረችበት ጊዜ የለም ። እግዚአብሔርም በረድኤቱ ከኢትዮጵያ የተለየበት ጊዜ የለም ።ለዚህም በቂ ምክንያት አለ ። ይኸውም በየጊዜው የሚነሱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት እግዚአብሔርን በመስበክ ህላዌ መለኮትን በመንገር ፣ እግዚአብሔር በፍጥረቱ ለፍጥረቱ እንዲታወቅ ምክንያት ስለሆኑ ነው ።

የዚህ ድርጅት ዓላማም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን ሐዋርያዊ ተልእኮ ጊዜው ከሚፈቅደው ሂደት ጋር በማገናዘብ መፈጸም ሲሆን ፣ ከማንኛውም ፖለቲካዊ ተግባር



ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው የጠ.ቤ.ክ. ዋና ሥራ አስኪያጅ ፤

ነፃ በሆነ መንገድ ከክርስትና ውጭ የሆኑትን ሕዝቦች ወደክርስትና በመመለስ ራሳቸውንም ወደእውቀት ጐዳና እንዲመሩ መርዳት ፣

፪ኛ/ ክርስቲያኑን ሕዝብ በሃይማኖትና በግብረ ገብነት ፣ በልማትና በጤና አጠባበቅ ራሱን እንዲረዳ መምራት ፣

፫ኛ/ በተቻለም መጠን ከኢትዮጵያ ውጭ ወንጌላውያንን ለመላክ ስለነበረ ይህ ሁኔታ በአንዳንድ ቦታዎች እየተፈጸመ በመሆኑ የድርጅቱ ሥራ እንደዓላማው እየተቃናለት ነው ማለት ይቻላል ።

ይህ ድርጅት ራሱን ችሎ ሕጋዊ አካልነት ኖሮት እንዲቋቋም ከተደረገ ወዲህ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አያሌ አገልግሎቶችን ፈጽሞአል ።

በዚህም መሠረት ከመስከረም ፩ ቀን ፲፱፻፶፮ ዓ-ም ጀምሮ እስከ ፲፱፻፷፰ ዓ-ም- በቀን ፴ ደቂቃ በአማርኛ ቋንቋ ብቻ ልዩ ልዩ መንፈሳውያን ትምህርቶችን ታሪካዊና ትምህርታዊ መልእክቶችን ለመላው ኢትዮጵያ ለምሥራቅ አፍሪካና ለመካከለኛው ምሥራቅ በቀድሞው ብሥራተ ወንጌል ራዲዮ ጣቢያ ሲያስተላልፍ ቆይቶአል ።

ድርጅቱ ሀገር አቀፋዊ ይዘት ስለአለውና የአድማጮች ፍላጐትም እየጨመረ በመሔዱ ከ፲፱፻፷፰ ዓ-ም ጀምሮ ፕሮግራሙን በማስፋፋት እና የተለያዩ ቋንቋዎችንም በመጨመር በሳምንት በ፷፩ ርዕሶች ፣

ሀ/ በአማርኛ ፣ ለ/በትግሬኛ ፣ ሐ በኦሮምኛ ፣ መ/ በግዕዝ በቀን ፫ ሰዓት እስከ መጋቢት ፫ ቀን ፲፱፻፷፱ ዓ-ም ድረስ በቀድሞው የብሥራተ ወንጌል ራዲዮ ጣቢያ ሲያስተላልፍ ቆይቶ ራዲዮ ጣቢያው ለበለጠ ሕዝባዊ አገልግሎት ወደ መንግሥት ሲዛወር በኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ግንቦት ፴ ቀን ፲፱፻፷፱ ዓ-ም በቁጥር ፩ሺ፯፻፬/መ፷/በ፩ በተጻፈ ትእዛዝ ቤተ ክርስቲያን ሥራ እየፈጠረች እንድታሠራ ስለተፈቀደ በዚሁ መሠረት ድርጅቱ ሥራውን አሻሽሎና በልዩ ልዩ ዝግጅቶች አከፋፍሎ እስከአሁን ድረስ ለስብከተ ወንጌል መስፋፋት ጥረት ሲያደርግ ቆይቶአል ።

<u>ብፁዕ ወቅዱስ አባታችን ፣</u>

<u>የተወደዳችሁ እንግዶች ፤</u>

ድርጅቱ የተለመደው ቃለ እግዚአብሔር እንዳይቋረጥ ለጥቂት ጊዜ ተቋርጦ የነበረውን ትንሣኤ መጽሔት በ፪ ወር አንድ ጊዜ በማሳተም ድምፀ ተዋህዶ ጋዜጣ ተሻሽሎና ብዛቱን ጨምሮ እንዲታተም በማድረግ ከመስከረም ፩ ቀን ፲፱፻፸ ዓ-ም እስከ ፲፱፻፸፩ ዓ-ም መጽሔቱ ከሁለት ወር ወደ አንድ ወር፣ድምፀ ተዋህዶ ጋዜጣ መጠኑ ከቀድሞው ከፍ ብሎ በወር መታተሙ ቀርቶ በየአሥራ አምስቱ ቀን እንዲታተም በማድረግ ትምህርት ፈላጊዎች ለሆኑ ምዕመናን በማቅረብ እስካሁን በማገልገል ላይ ይገኛል ።

፪ኛ/ ከተቋቋመበት ጀምሮ በክብረ በዓላት በዕለተ ሰንበት የወንጌል መምህራንን በመላክ ሲያስተምር ቆይቶ አሁንም ሰባክያንን በመጨመር የማስተማሩን ተግባር በይበልጥ አጠናክሮ የቤተ ክርስቲያንዋ ዓይነተኛ ተግባር ስብከተ ወንጌልን በማስተላለፍና ግዴታውን በመወጣት ላይ ይገኛል ።

፫ኛ/ ትምህርት ባልደረሰባቸው ክፍላተ ሀገር ትምህርት ቤቶችን አቋቁሞ ያለ ምንም ክፍያ በነፃ እስከአሁን ድረስ በማስተማር በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ተማሪዎችን ለሀገሪቱ ያፈራ ሲሆን እንዲሁም ፣ ፩ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀው ቀሪውን ለመጨረስ አቅም የሌላቸውን ተማሪዎች ወደ አዲስ አበባ በማምጣት እየረዳ አሁንም ያስተምራል ።

፬ኛ/ በከፋ ክፍለ ሀገር በማጂ አውራጃ ጨብራ በተባለው የወንጌል ትምህርት ፈጽሞ በሌለበት ቦታ ለልዩ ልዩ ብሔረሰቦች በቋሚነት አንድ የወንጌል መምህር መድቦ እስከአሁን ድረስ በማስተማር ላይ ይገኛል ። በዚህ ሥራ የረዱት ድርጅቶችና ግለሰቦች በዚህ አጋጣሚ ሊመሰገኑ ይገባል ።

፭ኛ/ ልዩ ልዩ የቤተ ክርስቲያን ዜማዎችን ፣ መንፈሳዊ መዝሙሮችን በገናዎችን ቅዳሴዎችን ፣ መንፈሳዊ ስብከቶችን በካሴት በማዘጋጀት በቋሚነት ለቅርስ አስቀምጦአል ።

፮ኛ/ መንፈሳውያን የወጣቶች የሰንበት ማኅበራትን በማቋቋም በተለይም ለመጀመሪያ ጊዜ ደናግልን በቤተ ክርስቲያን በማሰባሰብ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል ።

፯ኛ/ በውጭ አገር ከወዳጅ አብያተ ክርስቲያናት ጋር ግንኙነት በማድረግ የገንዘብ ርዳታ ለማግኘት ሲችል እንዲሁም በልዩ ልዩ ጉባኤዎች በመገኘት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህ ቤተ ክርስያንን በመወከል ከፍተኛ አገልግሎት ያበረከተ ሲሆን እንዲሁም ከወዳጅ አብያተ ክርስቲያናት ጋር በመጻጻፍ የነፃ ትምህርት በማስገኘት ከ፴ በላይ የሆኑ ምሁራንን አስተምሮ ለቤተ ክርስቲያን እና ለሀገሪቱም በማበርከቱ በቤተ ክርስቲያን ስም ለድርጅቱ ምስጋና አቀርባለሁ ።

እነዚህ ምሁራን አሁንም በሀገሪቱና በቤተ ክርስቲያንም ከፍተኛ ሥልጣን ይዘው በማገልገል ላይ ስለሚገኙ በዚህ በኩልም ድርጅቱ አገር አቀፍ ባለውለታ ነው ማለት ይቻላል ።

<u>ብፁዕ ወቅዱስ ሆይ !</u>

<u>የተወደዳችሁ የበዓሉ ተሳታፊዎች ፤</u>

<u>የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ</u> ሐዋርያዊ ድርጅት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ዓይነተኛ ዓላማ የሆነውን ቅዱስ ወንጌል ያለማቋረጥ ለሃያ ዓመታት ሲያስተምር ቆይቶ፣ ዛሬ ሃያኛ ዓመቱን ለማክበር መብቃቱ በተሐድሶ ላይ ለምትገኘው ቤተ ክርስቲያናችን የሥራ ዕድገትና መሻሻል አንዱ ምስክር በመሆኑ ቤተ ክርስቲያን በሥራው ትኮራብታለች ። ወደፊትም ለሚያደርገው የወንጌል ተልዕኮ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ማንኛውንም ዕርዳታ እንደምታደርግለት ቃል ስገባ ደስታ እየተሰማኝ ነው ።

ሌሎች ይህን መሳይ ድርጅቶችም እንዲኖሩና እንዲስፋፉ ማንኛውንም ጥረት በማድረግ የቤተ ክርስቲያኑዋ ሁለንተና ለሆነው የወንጌል ትምህርት ቅድሚያ በመስጠት የሚፈለገውን ሁሉ ለማሟላት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ጥረት እንደምታደርግ ስገልጽ በዚህ አጋጣሚ የተገኛችሁ ሁሉ ለዚህ ዓላማ መሳካት ትብብር እንድታደርጉ ስጠይቅ ባለሙሉ ተስፋ በመሆን ነው ።

ስለአዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ

እግዚአብሔር ይስጥልኝ

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ...

ከ፯ኛው ገጽ የዞረ

ፈት ሚኒስቴር በቁጥር ፩ሺ ፩፻፸፭/ ፷፻፯/፹ ከግንቦት ወር ፲፱፻፶፮ ዓ. ም. ጀምሮ ለአንድ ድራሲ በወር ሁለት መቶ ብር ፈቀደ። በዚህጊዜ የድርጅቱ በጀት ወደ አሥራ ስምንት ሽህ ብር ከፍ ሲል ሥራውም በዚያው መጠን ሊስፋፋ ችሏል ።

እንደገናም ድርጅቱ ሥራውን በይበልጥ እንዲያስፋፋና ዓላማውንም አጠንክሮ እንዲሠራ አስፈላጊ በመሆኑ ከመንግሥት በቁጥር ፪ሽ፬፻፸/ ፷፫/፶፮ ሐምሌ ፲ ቀን ፲፱፻፶፮ ዓ- ም- ለመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል አስተዳዳሪ በተጻፈ ትእዛዝ ከካቴድራሉ የወር (የቤት ኪራይ) ገቢ ላይ በየወሩ ፩ሺ፪፻፶ በዓመት ፷፫ሺ ቀድሞ ከቤተ ክህነት ከተፈቀደው ፲፰ሺ ብር ጋር በድምሩ ሰማንያ አንድ ሽህ ብር በጀት ተፈቅዶ ሥራው በይበልጥ እንዲስፋፋ ተደርጓል ።

<u>ድርጅቱ እንዲስፋፋ ያስፈለገበት</u>

<u>ዓ ላ ማ</u>

፩—የወንጌልን ትምህርት ለምእመናን ለማዳረስ

፪—የድርሰትና ሥነ ጽሑፍ ክፍልን አስፋፍቶ መንፈሳውያን ጽሑፎችን እያሳተመ ለክርስቲያኖች ለማቅረብ

፫—ጥንታዊውንና ዘመናዊውን ትምህርት አቀናጅተው የሚያስተምሩ ትምህርት ቤቶችን አቋቁሞ ያልተማሩ ኢትዮጵያውንን ለማስተማር ነው ።

፩ኛ/ <u>የወንጌል ትምህርት</u>

ተከታዩ በ፲፩ኛው ገጽ





www.ethiopianorthodox.org

# «ሒ ዱ ና  አ ስ ተ ም ሩ»

( በብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የሸዋ
ሀ/ስብከት ሊቀ ጳጳስ )

ይህ ትዕዛዝ የተሰጠው ለሐዋርያት ነው ትዕዛዙን የሰጠው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ። ዕለቱም የትንሣኤ ዕለት ነው ።

ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ ጌታችን የታየው ለዓማኞች ብቻ ነበር ። የነገራቸውም የደስታ መግለጫ ቃላት፤ ደስ ይበላችሁ ሰላም ለእናንተ ይሁን የሚሉ ናቸው በዚህ ደስ ብሏቸው ሳለ ይህ ደስታና ሰላም በእናንተ ለእናንተ ብቻ ስላልሆነ « ሂዱና አስተምሩ » ላልሰሙት አሰሙ ብሎ አዘዛቸው ሐዋርያት ይህ ትዕዛዝ ለጊዜው ከባድ መስሎ ሳይታያቸው አልቀረም ነገር ግን ትዕዛዙ ከላይ የመጣ ስለሆነ መልሱ እሺ ብቻ ነበር ። ደግሞም የሚያስተምሩት ድንገተኛ ነገር አልነበረም በዓይናቸው አይተው በጆሮአቸው ሰምተው በእጃቸው ዳስ ሰው የተረዱትን ዕውነት ነው ፤ ስለዚህ የሐዋርያት ምስክርነት አስፈላጊ ነበር «ማን ይገገር የነበር ፤ ማን ያርዳ የቀበር» ነውና መታዘዛቸውም በሚገባ ነው ።

በብሉይ ኪዳን ሕያው አምላክ ነቢያትን ለማስተማር ሲልክ ከተላኪዎቹ አንዳንድ ጥያቄ ይቀርቡለት ነበር ።

ለምሳሌ ሙሴን ወደ ፈርዖን በላከው ጊዜ በሙሉ ልቡ ፈቃደኛነቱን ገልጧል ነገር ግን አብራርቶ አቀላጭ ልጮ ለመናገር የማይችል የተባ ምላስ የሌለው መሆኑን ገልጦ በመናገሩ ይህን ችግር ለማራቅ ወንድሙ አሮን ትርጁማን እንዲሆነው ታዘዘ ሙሴም በትርጁማን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ አስተላለፈ ። ( ዘጸ ፫ ፡ ፲ )



ከጌታ ልደት ሰባት መቶ ዓመት ቀደም ብሎ የነበረው የይሁዳ ነቢይ ኢሳይያስም ከዕለታት አንድ ቀን ሕያው አምላክ ወደ ሕዝቤ ማንን ልላክ እያለ ሲያማርር ሰምቶ ( ኢሳ ፮ ፡ ፰ ) ለዚህ ጥሪ ፈቃደኛነቱን ቢገልጥም የነበረበትን ጉድለት አልደበቀም ከእግዚአብሔር የሚደበቅ ምንም ነገር የለምና «ከንፈሬ ለምጻም ነው» ያንተን ቅዱስ ስም ለመጥራት አልችልም አለው በዚህ ጊዜ ሕያው አምላክ በሰማያዊ ማኅየዊ እሳት ለምጹን ተኮሰለት ኮልቶ አንጥሮ ቀድሶ ላከው ኢሳይያስ ከዚያ በኋላ ወደኋላው አልተመለሰም ። የተላከበትን አደረሰ ።

ሐዋርያት ይህን ትዕዛዝ ሲታዘዙ ያቀረቡት ጥያቄ መኖሩን ወንጌል አልተናገረም ። ነገር ግን ትዕዛዙን የሰጣቸው እርሱ ትዕዛዙን በሥራ ለማዋል ከመነሳታቸው በፊት የሚያስፈልጋቸው ነገር መኖሩን አልሰወራቸውም ። አዲሱን ትዕዛዝ ለማስተላለፍ አዲሱን ትምህርት ለማስተማር የሚለበስ የክብርና የጌጥ ልብስ (ዩኒፎርም) ሰማያዊ ኃይልን እስከሚለብሱ ድረስ እናስተምር ብለው ወዲያና ወዲህ እንዳይሉ አበክሮ ነግሯቸው ነበር ።

ከአሮን ጀምሮ በብሉይ ኪዳን የተሾሙ የእሥራኤል ካህናት በሚሾሙበት ጊዜ የሚለብሱት ኤፉድ የሚባል ቀሚስ (ልብሰ ተክህኖ) ነበራቸው (ዘጸ ፳፰ ፤ ፫—፬) ኤፉድ ለብሰው ኡሪምንና ቱሚምን በደረታቸው አጥልቀው ነበር የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ለሕዝቡ የሚያስተላልፉ ፤ የሚጸልዩ መሥዋዕት የሚያቀርቡ ይህ ልብስ ለነዚያ ካህናት ክብርም ነበር ጌጥም ነበር ። በዚህ ግሥ ነው ጌታ ለደቀመዛሙርቱ ሰማያዊ ኃይልን እስኪለብሱ ወዲያና ወዲህ እንዳይሉ ያዘዛቸው በበዓለ ጰንጠቆስጤ ፤ ይህን ሰማያዊ ኤፉድ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ከለበሱ በኋላ ሐዋርያት የጨለማውን በብርሃን ፤ የሹክሹክታውን በስገነት ላይ ሆነው አስተጋቡት ። በልሳናቸውም ለምጽ ፤ ወይም መንተባተብ ስለሌለባቸው ስሙኝ ስሙኝ የሚያሰኝ ለዛ ነበራቸው ።

ሐዋርያት ወዴት ሂደው አስተማሩ? ብሎ የሚጠይቅ እንግዳ ሰው ቢኖር መልሱ በኃጢአት የታሠሩ ነፍሳት ወዳሉበት ነዋ የሚል ነው ። የጌታቸውም ጉዞ ወደዚያው ነበርና ( ቀዳ ጴጥ ፫ ፡ ፲፱) በብርሃን ትምህርታቸው ጨለማን እንዲያስወግዱ ጨለማ ወደ ሰፈነበት ቦታ ላካቸው ። በዕውነትም ትምህርታቸው ሐሰትን እንዲያሸንፉ ሐሰት ወደ ሠለጠነበት ቦታ ላካቸው። በሰላማዊ ትምህርታቸው እርቅና ሰላምን እንዲመሠርቱ ብጥብጥ ሁከትና ሽብር ወደበዛበት ቦታ ላካቸው ። በኃጢአት የባርነት ቀንበር ሥር ሆነው ለሚኖሩ ነፃነትን ፤ ተገፍተው ለሚኖሩ እኩልነትን እንዲሰብኩ ላካቸው ይህንን ትዕዛዝ ለመፈጸም ሐዋርያት ባደረጉት ጉዞ ማለት የትንሣኤንደስታ፤ የትንሣኤን ሰላማዊ መልእክት ፤ በትንሣኤም የተገኘውን ነፃነትና እኩልነት ለመሰበክ ባደረጉት ጉዞ ብዙ መከራና ሥቃይ ተቀብለዋል ። ይሁን እንጂ የቃላቸው ወላፈን ግብዙን ሕይወት እያፈራረሰ በመጣል ዕውነተኛውን ሕይወት መሥርቷል ። ስለ ሰው ልጅ እኩልነት የማያምን የነበረው የሮማ መንግሥት እንኳ ሳይቀር እንዲያምን ተደርጓል ።

እግዚአብሔር የሰውን ዘር ከፈጠረ ጀምሮ የራቁትን ለማቅረብ የቀረቡትንም ለመመገብ የሚጠቀምበት መሣሪያ ትምህርት ነው ። በብሉይ ኪዳን አስተማሪዎችን ይፈልግ ነበር ያሰማራም ነበር ማስተማሪያ መጻሕፍትንም ሲሰጥ ኑሯል ። በአዲስ ኪዳንም ራሱ በመምህርነት ተገለጠ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር አስተማረ ። የሚያስተምሩ ሐዋርያትንም ሾመ ። ሐዋርያትም ሕይወታቸውን ሳይቆጥቡ የተረከባቸውን ያህል አስተማሩ አሁን ቤተ ክርስቲያን ይዛው የምትጓዘው ከምላጉደል የሐዋርያትን ትምህርት ነው ።

ዛሬም እግዚአብሔር መምህራንን እየፈለገ ነው ምዕመናንም የመምህራን ያለህ እያሉ ነው ። ዛሬ ማነው እንደ ኢሳይያስና እንደሙሴ ጉድለቱን ለእግዚአብሔር ነግሮ በረከትን ተቀብሎ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ለመፈጸም ጉዞውን የሚጀምር ፤ ዛሬ ማነው እንደ ሐዋርያት ሦስት ዓመት ከሦስት ወር የሃይማኖት ትምህርት አጥንቶ ከጨረሰ በኋላ ወደ ማስተማር ሥራ የሚላክ ። እግዚአብሔር ዛሬ «ሂዱና አስተምሩ» እያለ ይጮኻል ። ዛሬ በዓለማችን ካለው ሕዝብ አብዛኛው በኃጢአት እግረ ሙቅ የታሠረ ነው ። የሚፈታው ይፈልጋል ፤ በውሸት በሌብነት በአልኮል መርዝ በዝሙትና በቃኝ ባለማለት የተተበተበ ነው ። ይህንም ሰብአዊ በሽታ ሊፈውሰው የሚችለው ቤተ ክርስቲያን የምታስተላልፈው የትንሣኤ መልእክት ነው ። የሰውን ሕይወት አፍኖ የያዘው የኃጢአት ጭጋግ ሊገፍ የሚችለው የቤተ ክርስቲያን የድምጽዋ ብርሃን ሲፈነጥቅበት ነው ።

ስለዚህ ነው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊ ድርጅት የተቋቋመው ። በውነቱ ይህ ድርጅት ገና የሐያ ዓመት ወጣት ቢሆንም የሠራው ሥራ ከጐልማሶች አስቁጥሮታል ዕድሜ ቢረዝም ካልሠሩበት ያስወቅሳልና ። ቤተ ክርስቲያናችን ከአምላኳ የተቀበለችውን ትእዛዝ በሥራ ለማዋል እንደነዚህ ያሉ ድርጅቶችን መውለድና ማሳደግ ግዴታዋ ነው ።

ኤፉድ መንፈስ ቅዱስን የለበሰ ቅዱስ ሲኖዶሳችንም «ሂዱና አስተምሩ» በሚለው አምላካዊ ትዕዛዝ መሠረት የመዳን ወንጌልን ካልደረሰበት ለማዳረስ ማሠልጠኛዎችንና ከፍተኛ ትምህርት ቤቶችን ከፍቷል ። ወንጌልን ወዳልደረሰበት ማዳረስና በደረሰበትም ማጠናከር የሚቻልበትን ዘዴ በሚያጠናው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ክፍል (C.W.M.E. "Commission on World Mission and Evagelization)

ቤተ ክርስቲያናችን አባል ስለሆነች ሩማንያ ዋና ከተማ ቡካሬስት ላይ (በ፲፱፻፸፫ ሚያዚያ) በተደረገው ስብሰባ ለዚህ ተግባር በኢትዮጵያ በኩል እንደ ምሳሌ ሆኖ የተወሳው ይህ ሐዋርያዊ ድርጅት ነው በውነቱ ይህ ድርጅት ለቤተ ክርስቲያን አኩሪና አስመስጋኝ ስለሆነ ተርፎ ለሚቀረው ዕድሜ አይንፈገው እንላለን ።

---

## የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ...

ከ፱ኛው ገጽ የዞረ

በዚህም ዓላማ ቀደም ሲል በብሥራተ ወንጌል ራዲዮ ጣቢያ ድርጅቱ ያስተላልፈው ከነበረው መልእክት

ሀ— በመቶ ሠላሳ እጅ መንፈሳዊ ዝግጅት ለክፍላተ ሀገርና ለአዲስ አበባ አካባቢ በቀን የ፴ ደቂቃ ትምህርት ያቀርብ ነበር ፤ ቅዱስ መጽሐፍ «አስቀድሞ የእግዚአብሔርቃል ለእናንተ ይነገር ዘንድ ይገባል»የሐዋ ፲፫ ፡ ፵፮ እንዲሁም በሌላ አንቀጽ «ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም፤ ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣም ቃል እንጂ» ማቴ ፬ ፡ ፬ ስለሚል በዚህ መሠረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት ከማነኛውም ተግባር ሁሉ ለእግዚአብሔር ቅዱስ ቃል ቅድሚያን ይሰጣል ሌላውንም ያስከትላል ።

ለ— ሰባ በመቶ እጅ ልማት መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ«አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ ሌላው ሁሉ ግን ይጨመርላችኋል» እንዳለ ማቴ- ፮ ፡ ፴፮ ድርጅቱ መጽሐፍ ቅዱስን ብቻ ሳይሆን ልማት ነክ ነገሮችንም ያስተምራል ፤ ጌታችንና መድኃኒታችን ወንጌልን ብቻ አስተምሩ አላለም «ድውያንንም ፈውሱ» ብሏል ፤ ይህንንም በማመን ድርጅቱ የልማት ፕሮግራም እያዘጋጀ ስለ ጤና አጠባበቅ ፤ ስለ አካባቢ ንጽሕና በጠቅላላ በሽታን ስለመከላከል ሁሉ ያስተምራል ። እንዲሁም ስለ ትምህርት ዕድገት ልዩ ልዩ ዝግጅቶችን ያቀርባል።

በዚህ የትምህርት ዕድገት ዝግጅት ማነኛውም ሰው መማር ማንበብና መጻፍ እንዲችል በልሳን መናገርም ለወንጌል ሥራና ለልማት ጠቃሚ እንደሆነ በቃልም ፤ በግብርም ያስተምራል ። መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከድንቁርና እንዲላቀቅ የትምህርትን ጥቅም ያስተምራል ። አንድ ሕዝብ ነፃነት ሊኖረው የሚችል በትምህርት ስለሆነ ትምህርት በሀገሪቱ እን





www.ethiopianorthodox.org

ዲያድግና እንዲስፋፋ ዘወትር ይጥራል ።

በልማት ረገድ ያለው የድርጅቱ ተግባር ይህ ብቻ አይደለም ፤ በጠቅላላ ስለ ማኅበራዊ ኑሮም ዝግጅት ያቀርባል ፤ በየዕለቱም ከሕዝቡ ጋር በቅርብ እየተገናኙና እየተዋወቁ የኅብረተሰቡን ችግር በመመልከት በመገናኛ ዘዴዎች ትምህርትን የሚያስተላልፉ የድርጅቱ የሥራ ክፍሎች በተቻለ መጠን በትጋትና በቅልጥፍና ይሠራሉ ።

ድርጅቱ ባሉት የሥራ ክፍሎችና የትምህርት ማሠራጫ ዘዴዎች ሁሉ ለማኅበራዊ ኑር አስፈላጊውን ምክርና ትምህርት ይሰጣል ። ቤተ ክርስቲያንም በማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ ምን ዓይነት የሥራ ድርሻ እንዳላት በመግለጥ ሕዝቡን ከቤተ ክርስቲያን ፤ ቤተ ክርስቲያንንም ከሕዝብ ጋርያስተባብራል ። «እናንተ የምድር ጨው ናችሁ . . . እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ » በተባለው አምላካዊ ቃል መሠረት በማኅበራዊ ኑሮ በኩል ያለውን ግዳጅ ለመፈጸም ከልብ ይጥራል



አቶ አእምሮ ወንድም አገኘሁ ድርጅቱን ከ፲፱፻፶፱—፲፱፻፷፫ በዋና ሥራ አስኪያጅነት የመሩ ።

ይሁን እንጂ ይህን ሁሉ ሲሠራ ብዙ ችግሮች ሳያጋጥሙት አልቀረም ። ቢሆንም ከአገር ውስጥና ከአገር ውጭ በሚያገኘው የሐሳብና የቁሳቁስ ድጋፍ ችግሩን እያሟላ የወንጌልና የልማት ሥራውን ሊያስፋፋ ችሏል።



ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው ድርጅቱን ከ፲፱፻፷፫-፲፱፻፷፭ በሥራ አስኪያጅነት የመሩ አሁን የጠ. ቤ. ክ. ዋና ሥራ አስኪያጅ ፤

ይህ ድርጅት ከ፲፱፻፶፮-፲፱፻፷፰ ዓ.ም. ድረስ የወንጌልና የልማት ዝግጅቱን ለምእመናን ያስተላልፍ የነበረው በአማርኛ ቋንቋ ነው ። ይኸውም በጥዋትና በማታ ክፍለ ጊዜ በአጭርና በረጅም ሞገድ ለ፴ ደቂቃ ነበር ።

## ፪- የድርሰትና ሥነ ጽሑፍ ክፍል

ይህ ክፍል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ሥርዓት መሠረት ጋዜጦችንና መጽሔቶችን እንዲሁም ለሕዝብ የሚጠቅሙ ጽሑፎችን ከቤተ ክርስቲያን ቋንቋ ወደ አማርኛ ቋንቋ እየተረጐመ በማሳተም ለሕዝብ የሚያቀርብ ክፍል ነው ። ይህም ክፍል በአራት ንኡሳን ክፍሎች ይመደባል ።

ይኸውም ፥-ሀ.ድምፀ ተዋሕዶ ጋዜጣ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት በየወሩ የሚያሳትመው « ድምፀ ተዋሕዶ » የተሰኘ ጋዜጣ ነበረው ። አሁንም አለው ይህ ጋዜጣ ለመጀመሪያ ጊዜ የታተመው በ፲፱፻፶፮ ዓ. ም. በሚያዝያ ወር ሲሆን ፤ ጋዜጣው ጥንታዊ የሆነችውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እምነት ፤ ባህልና ሥርዓት ለማሳወቅ ይዘጋጃል ። ይህ ብቻም አይደለም ። ድርጅቱ በጠቅላላ የሚፈጽማቸው ሥራዎች ሁሉ በየጊዜው በዚሁ ጋዜጣ እየተዘጋጁ ይቀርባሉ ፤ ጋዜጣው በቀላል ቋንቋ ፤ በአጭር ዓረፍተ ነገርና በተጣሩ ቃላት ስለሚታተም ለሊቃውንት ለተራ አንባብያንና ለቤተ ሰብእ ሁሉ ጠቃሚና ተወዳጅ ነው ። ጋዜጣው በመጀመሪያ ጊዜ ሲታተም ባለ ፲፪ ገጽ ነበር ። በኋላ ግን መጠኑ ከፍ እንዲልና ባለ ፰ ገጽ እንዲሆን ተደርጓል ።

### ለ. « ትንሣኤ » መጽሔት

«ትንሣኤ» ለመጀመሪያ ጊዜ የታተመው የካቲት ፲ ቀን ፲፱፻፶፰ ዓ.ም. ነው ። « ትንሣኤ » በመጀመሪያው እትሙ በተለያዩ አርእስት የተዘጋጁ ጽሑፎችን ይዞ በ፴፮ ገጽት ለአንባብያን ቀረበ ።



አቶ ዘመድሁን ብዙ ወርቅ ድርጅቱን በተጠባባቂነትና በዋና ሥራ አሥኪያጅነት ከ፲፱፻፷፭-፲፱፻፸፬ የመሩና ከድርጅቱ መሥራች ሠራተኞች አንዱ ፤

«ትንሣኤ» በዓመት ሦስት ጊዜ ብቻ ይታተም ነበር ፤ መጽሔቱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንን መንፈሳዊ የሥራ እንቅስቃሴና እርምጃ ስለሚገልጽ «ትንሣኤ» ተብሎ ተሰይሟል ። መጽሔቱ በከፍተኛ ጥናትና ምርምር ስለሚዘጋጅ በቤተ ሰብእና በሊቃውንትም ዘንድ ተወዳጅነት አለው ። ይህ ተወዳጅነት ያለው መጽሔት በበጀት ችግር ምክንያት አንዳንድ ጊዜ በመቋረጡ አንባቢዎች ቅር ይሰኙ እንደነበረይታወሳል ። ይህም ይሆን የነበረው ከ፲፱፻፷፱ ዓ.ም. በፊት ነው ። በአጠቃላይ ድምፀ ተዋሕዶ ጋዜጣና ትንሣኤ መጽሔት ይዘዋቸው የሚወጡ ጽሑፎች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እምነትና ሥርዓት የሚያስተምሩ ፤ ምዕመናንን በሥጋዊና መንፈሳዊ ሕይወት የሚያድሱ ለማኅበራዊ ኑሮ ጠንቅ የሆኑ ነገሮችን የሚያስወግዱና ለማኅበራዊ ኑሮ የሚጠቅሙ ናቸው ።

ሐ—ልዩ ልዩ አጫጭር የታሪክ ጽሑፎች—ድርጅቱ አጫጭር መንፈሳውያን ታሪኮችና ምሳሌዎች ያሉባቸውን ጽሑፎች እያዘጋጀ በሚያስተምርበት ሁሉ ያዳርሳል ። ልዩ ልዩ መጻሕፍትንና ለመሠረተ ትምህርት የሚያገለግሉ አጫጭር እትሞችን እያዘጋጀ በነፃና በመጠነኛ ዋጋ ለሕዝብ ያቀርባል ። ይህ ዓይነቱ ጽሑፍ ማንበብና መጻፍ ለሚችሉ የማንበብና የመጻፍ ችሎታቸውን ለማሻሻል ገና ማንበብና መጻፍ ላልቻሉ እንዲያነቡና እንዲጽፉ ለማድረግ እጅግ ይጠቅማል ። በእነዚህ እትሞች አንዳንድ ጊዜ የድርጅቱን ዓላማ የሚገልጡ ሥዕሎችና ዜናዎችም ይወጡ ነበር።

እንዲሁም ስለ ግብረ ገብነትና ስለ ልዩ ልዩ መንፈሳዊና ሥጋዊ ሕይወት የሚያስተምሩ መጻሕፍትን ከተለያዩ የውጭና የአገር ውስጥ ቋንቋዎች እየተረጐመ በማሳተም ለአብያተ ክርስቲያናትና ለምዕመናን ያዳርሳል ። ድርጅቱ ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ጽሑፎች ሲያዘጋጅና ለሕዝብ ሲያዳርስ ኪሣራ እንጂ ትርፍ አያገኝም ። ቢሆንም የተቋቋመበት ዓላማ በነፃ ለማስተማር እንጂ ለትርፍ ስላልሆነ በሚገጥመው የገንዘብ ኪሣራ አይፀፀትም ። ከዚህ በላይ በተገለጸው መሠረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት ከተቋቋመበት ከ፲፱፻፶፮-፲፱፻፷፯ ዓ.ም.



የአሁኑ ሥራ አስኪያጅ አቶ ሐዲስ ተረፈ

በቀን የ፴ ደቂቃ በወር የ፲፭ ሰዓት በዓመት የ፩፻፹ ሰዓት ፤ በዘጠኝዓመት የ፩ሺ፮፻፳ ሰዓታት ትምህርት በአዲስ አበባና በገጠረ ኢትዮጵያ ለሚኖሩ ክርስቲያኖች አስተላልፎአል ።

እንዲሁም ድምፀ ተዋሕዶ ጋዜጣ ከ፲፱፻፶፮ ሚያዝያ ወር ጀምሮ እስከ ፲፱፻፷፯ ድረስ በወር አንድ ጊዜ በ፩ ሽህ ብዛት እየታተመ ለአንድ ዓመት በነፃ ይታደል ነበር ፤ ከዚያ በኋላ ግን በ፴፱ ሳንቲም እያሳተመ በ፲ ሳንቲም ለሕዝብ ማከፋፈል ጀመረ። በዚህም መሠረት ከ፲፱፻፶፮—፲፱፻፷፯ ዓ. ም. (ከአንድ መቶ ሠላሳ ሽህ በላይ የጋዜጣ እትሞችን ለምዕመናን አከፋፍሏል ። የትንሣኤ መጽሔት ግን አንዳንድ ጊዜ ይቋረጥ ስለ ነበረ ከተጀመረበት ከ፲፱፻፶፰—፲፱፻፷፯ ዓ. ም. ሰባት ጊዜ የታተመ ሲሆን ፤የቅጂም ብዛት አሥራ ሁለት ሽህ ያህል ይሆናል ።

በሥነ ጽሑፍ ክፍል ከዚህም ሌላ የሚከተሉትን ጽሑፎች አዘጋጅቶ በማሳተም ለአንባብያን አዳርሶአል ።

፩— ስብከት በራዲዮ የተላለፉትን ጽሑፎች በጊዜው የራዲዮ ፕሮግራሙን ለማዳመጥ ዕድል ላልገጠማቸውና ሰምተውም የሰሙትን በጽሑፍ ለማግኘት የሚፈልጉ ሁሉ በመጽሐፍ መልክ ታትሞ ቢቀርብ ጠቃሚ መሆኑ ስለታመነበት ከ፲፱፻፶፮—፲፱፻፶፰ በራዲዮ የተላለፉት መልእክቶች በ፲፱፻፶፰ ዓ. ም. ታትመው ለምእመናን በመዳረስ ላይ ይገኛሉ።

፪— መዝሙር የድርጅቱ ደራስያን ያዘጋጁት መዝሙር ለመጀመሪያ ጊዜ በሁለት ሽህ ኮፒ ታትሞ ከተዳረሰ በኋላ ለ፪ኛ ጊዜ በ፲፱፻፸፬ ዓ.ም. ታርሞና ተሻሽሎ በሁለት ሽህ ብዛት ታትሞ ለምእመናንና ለመንፈሳውያን ወጣት ማኅበራት በመዳረስ ላይ ይገኛል ።

፫— የሐዋርያዊ ድርጅት የሥራ ዝርዝር በ፲፱፻፷ ዓ. ም.

፬— ስለ ቅዱስ ጳውሎስ ማንነት በ፷፪ ዓ.ም. ሁለት የሮማ ወታደሮች የተጻጻፉት ደብዳቤ (ትርጉም)

፭— የማኅበረ ድምፀ ተዋሕዶ ደንብ

፮— ግብረ ልኡካን ጥር ፫ ቀን ፲፱፻፷ ዓ. ም.

፯— የሴት ልጅ ዕድገት በሃይማኖት ፲፱፻፶፰ ዓ. ም.

፰— እኛና ባህላችን በእናት አገራችን «ግጥም»

፱— ይፈለግ መድኃኒት »

፲— የወርቅ ቀለበት »





www.ethiopianorthodox.org

፲፩—የአካል ክፍሎች አድግ ግጥም
፲፪—የጀግኖች ወኔ »
፲፫—ምክር ለወጣቶች »
፲፬—ሐዋርያነት
፲፭—የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በ፲፱፻፷፪ ዓ· ም·
፲፮—የጾም አስፈላጊነት በ፲፱፻፷፫ ዓ· ም·
፲፯—የልደት ታሪክና ክብረ በዓል አጭር ጽሑፍ
፲፰—የትንሣኤ በዓል » »
፲፱—መሠረተ እምነት በ፲፱፻፷፫ ዓ· ም·
፳— የጸሎት መጽሐፍ ሁለት ጊዜ
፳፩—የማኅበረ ክርስቶስ መተዳደሪያ ደንብ
፳፪—የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በ፲፱፻፷፬ዓ· ም· የተሰኙና በተለያዩ ሊቃውንት የተደረሱ ጽሑፎችን አሳትሞ ለአ



የድርጅቱ ሠራተኞች ስለ ድርጅቱ የወደፊት ዓላማ ሲወያዩ ፤

ንባብያን አቅርቧል ። ጽሑፎቹም ስለ ማኅበራዊ ኑሮ ወቅታውያን ችግሮች ፤ ስለ እምነትና ሥነ ምግባር የሚያስተምሩ ፤ ለታሪክና ጥናት ተመራማሪዎች ሁሉ የሚጠቅሙ የጥናት ጽሑፎች ናቸው ።

ክ ፍ ል ፪ ፤

# የድርጅቱ የራዲዮ ፕሮግራም መስፋፋት

የኢትዮጵያ ምእመናን ኑሮአቸውን እንዲያሻሽሉ ከኑሮ ውድቀት ወደተሻለ የኑሮ ሕይወት እንዲመሩ ሥራም የሰው ልጆች በረከት እንጂ ርግማን አለመሆኑን አምነው ለበለጠ ሥራ እንዲሰለፉ ለማድረግ የሚረዳና ወቅቱን የተከተለ መልእክት ለማስተላለፍ ታስቦ በመቶ ሠላሳ መንፈሳዊ መልእክት በመቶ ሰባ ልማት ነክ ዝግጅቶችን በማስተላለፍ ፤ እንዲሁም በመንፈሳዊ ኑሮአቸው እግዚአብሔርን በማምለክ ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ ግዴታን ለመወጣት እንዲችሉ ታስቦ የተደረገ መሻሻል ነው ።

በዚህ መሠረት ከግንቦት ፳፬ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ· ም· ጀምሮ እስከ መጋቢት ፫ ቀን ፷፱ ዓ· ም· ድረስ በሚከተሉት አርእስት በቂ የሆኑ ዝግጅቶችን አስተላልፎአል ።

## ፩- የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራዎች፤

በርእሱ እንደተመለከተው መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት በማድረግ በክርስቲያን ዓለም ውስጥ በክርስቶስ የተፈጸሙትን ተአምራት ለምእመናን የሚገልጽ ዝግጅት ነበር ።

## ፪- የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት

የተነበበውን የእግዚአብሔር ቃል መሠረት በማድረግ የጥቅሶቹን ትርጉም በማብራራት ለምእመናን የሚተላለፍ መንፈሳዊ ወይም ሃይማኖት ነክ ዝግጅት እንደነበረ ግልጽ ነው።

## ፫- የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

ሃይማኖት ነክ ዝግጅት ሲሆን፤አድማጮች በየጊዜው እየተከታተሉ የመጽሐፍ ቅዱስን ትርጉም እንዲያጠኑ የሚያደራጅ ዝግጅት ሆኖ ነበር የሚቀርበው ።

## ፬- ሴቶች በቤተ ክርስቲያን ፤

ይህ ዝግጅት ሃይማኖት ነክ ዝግጅት ሲሆን ፤ሴቶች በቤተክርስቲያን በኩል ያላቸውን ተሳትፎ የሚገልጽና የሚያበረክቱትን መንፈሳዊ ተግባር የሚያዘጋጅ ነው ።

## ፭- ሥነ ምግባር

ይህም ዝግጅት ሃይማኖት ነክ ከመሆኑም በላይ ፤ የሰው ልጆችን ምግባራዊ ይዞታ የሚያንፅ ግብረ ገብነትን የሚያስረዳ አዲሱ ትውልድ በመልካም ምግባር ተመርቶ ሀገሩንና ዜጋ

ተከታዩ ወደ ፲፯ኛው ገጽ ዞሯል



# በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መድረክ የሥነ ጽሑፍ ታሪክ

(ከብፁዕ ዶ/ር አቡነ ገሪማ
በሱዳን የኢ/ ኦር/ ተ/ ቤ/ ክ/ ጳጳስ፤
ከድርጅቱ መሥራች ሠራተኞች አንዱ)

ሥነ ጽሑፍ ዓይን ያየውን ፣ ጆር የሰማውን ፣ በአንደበት የተነገረውን በሐሳብ የመነጨውንና አእምሮም በማመዛዘን የተመለከተውን በርቀት አቅርቦና አጉልቶ የሚያሳይ ከስነ ጥበባት አንደኛው ክፍል ነው ።

ስነ ጽሑፍ የተገኘውና የሚገኘው ከትምህርት ዓለም ሲሆን ፤ ዓለምከተፈጠረ ዘመን ከተቆጠረ ጀምሮ የሰው ልጅ ያደረገው ምርምርና ጥናት ሊገኝ የቻለውና የሚችለው ከስነ ጽሑፍ ዓለም መሆኑ ግልጽ ነው ።

«በመጽሐፍ ያለ ይወረሳል ፣ በቃል ያለ ይረሳል» እንደሚባለው ሁሉ ማንኛውም ነገር በስነ ጽሑፍ መልክ ሰፍሮ በመረጃነት ቀርቦ የሚታይ ከመሆኑም በላይ ሊቃውንት የደከሙበት የምርምር ውጤትም በስነ ጽሑፍ ሕግና ሥነ ሥርዓት ተመዝግቦ በመጽሐፍ መልክ ተጠርዞና ተደጉሶ እንዲነበብ ለማድረግ የሚቻለውም በዚሁ አንፃር መሆኑ የታወቀ ነው ።

ጥልቀት ፣ ርቀትና ምጥቀት ያለው ሐሳብ በማፍለቅ ለሰሚው ፣ ለተመልካቹና ለአንባቢው የተጣራና የተስተካከለ ስነ ጽሑፍ ከነፍሬ ሐሳቡ ማቅረብ የሚቻለውም አንደኛ ብቃትና ፍጹምነት ያለው ቅዱስ አባት በመንፈስ ቅዱስ እየተመራ የእግዚአብሔር አፍ ሁኖ በመናገርና በማስተማር የተነገረውንም ትምህርት በመጻፍ ፣ ሁለተኛም በጥንታውያንና ዘመናውያን የስነ ጥበብ ቋንቋዎች የተጻፉትን ደህና አድርጎ በማንበብና በመተርጐም አገናዝቦና አሳክቶ መጻፍ ሲቻል ነው ። የጥንት ሰዎች የከበረ አእምሯቸው በከበረና በዳበረ ዕውቀቱ ያፈለቃቸው ጥበባት በመጻሕፍት አምዶች ላይ ተመዝግበው ለመገኘት ፣ ለመታየትና ለመነበብ የቻሉት በነዚያ ጥንታው



ያን አበው ጥረትና ተጋድሎ መሆኑን እናውቃለን ።

በዚህ ዓለም ታላላቅ የስነ ጥበብ ተግባር የፈጸሙ የታሪክ ሰዎች ምንም እንኳን ፈራሹ ሥጋቸው በሙታን ከተማ በመቃብር ለመኖር ቢገደድም የጊዜ ሩጫና ግልምጫ ሳይደመስሰው የማይሞተው ስማቸው ከመቃብር በላይ ሁኖ የሚመሰገነው ወደር በማይገኝለት የስነ ጽሑፍ ሥራቸው መሆኑን እንገነዘባለን ።

ጥንታውያን አሲሮ—ባቢሎናውያንና ግብፃውያን ስነ ጽሑፍን በሸክላ በቅጠል ፣ በአጥንትና በመሳሰሉት ቀርጸውና ጽፈው ማኖር ከጀመሩበት ዘመን አንስቶ እስከ አሁን ያሉት ጥበባት በስነ ጽሑፍ ተመዝግበው ይገኛሉ ።

በዚሁ አንፃር ጥንታውያን አሲሮ ባቢሎናውያንና ግብፃውያን በስነ—ጽሑፍ የአመጣጥ ታሪክ በዓለም አንደኛውንና ከፍተኛውን ቦታ የያዙ ሲሆን በይቀጥላልም የታወቀ የግሪኮ—ሮማን ስነ ጽሑፍ መሆኑን ታሪክ ያስተምረናል ።

ታላቁ የግሪክ ሀገር ደራሲ ሆሜር ከተቀኛቸው አንዷት ፊደል እንኳን ሳትጐድል ለሦስት ሺህ ዘመናት ያህል በመኖር ዛሬም የሰውን ልጅ አእምሮ በማርካት ላይ ይገኛል ።

በሆሜር ዘመንና ከዚያም ወዲህ በየጊዜው በከበሩ ደንጋዮች የተሠሩት ሕንፃዎች ሁሉ በዘመናት ጉሮሮ ተውጠው በዘመን ብዛት እንዳልነበሩ ሲሆኑ ፣ የዕውቀት አእማድ የሆኑት የስነ ጽሑፍ ቅርሶች ግን የዘመኑ ሩጫና ግልምጫ ሳይደፍራቸው ኗሪነት ያላቸው መሆናቸውን አሳውቀዋል ። በሌላም በኩል ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ፯፻፵—፯፻፹፭ የነበረው ታላቁ ነቢይ ኢሳይያስ «እነሆ ድንግል ትጸንሳለች ፣ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፣ ስሙንም አማኑኤል ትለዋለች - - » ይላል (ትንቢተ ኢሳይያስ ፯ ፣ ፲፬ ማቴ ፩፣፳፫) ይህም ክርስቶስ ከድንግል እንደሚወለድ ቀድም ሲል በነቢይ የተየተነገረና የተመዘገበ ትንቢትንና ስነ ጽሑፍ ነበር ።

ብሉይ ኪዳኑ የሐዲስ ኪዳኑ መነሻ እንደመሆኑ በነቢዩ በኢሳይያስ ትንቢት መነሻነት ከወንጌላውያንም አንዱ የሆነው ሐዋርያው ዮሐንስ «ሎጎስ» (ቃል) የሚለውን የግሪክኛ አባባል ወስዶ በስነ ጽሑፍ ወይንም በወንጌሉ መጀመሪያ ላይ ስለ ቃለ እግዚአብሔር ወልድ ሰው መሆን ገለጻ በማድረግ ተጠቅሞበታል ። በዚህም ስነ ጽሑፍ የተማረውም ሆነ ያልተማረው ዓለም ስለምሥጢረ ሥጋዌ በበለጠ ለመማርና ለማወቅ ችሏል ።

ከጊዜ በኋላም ጊዜው ሲደርስ በጊዜውጊዜ አምላክ ሰው ሆኖ ከቅድስት ድንግል ማርያም በመንፈስ ቅዱስ ተወልዶና አድጎ የሰውን ሕይወት ከሞት ወደ ሕይወት ፣ ከሲኦል ወደገነት ፣ ከኃጢአት ወደሥርየትና ልጅነት ለመመለስ በቀራንዮ በዕፀ መስቀል ላይ በተሰቀለ ጊዜ በሦስት ታላላቅ የስነ—ጽሑፍ ቋንቋዎች ማለት በዕብራይ



www.ethiopianorthodox.org

ስጥ ፣ በዕርዕና በሮማይስጥ «ኢየሱስ ናዝራዊ ንጉሠ አይሁድ» የሚል ተጽፎ ክርስቶስ በተሰቀለበት ዕፀ መስቀል አናት ላይ ተለጥፎ መነበቡ አይሁድን በበለጠ አስቆጥቷቸው ነበር ። በዚያን ጊዜ በነዚያ ሦስት ታላላቅ የእምነትና የስነ ጥበብ ቋንቋዎች የተጻፈው ስነ—ጽሑፍ በጊዜው በክርስቶስ መስቀል አናት ላይ ተለጥፎ ሊነበብ መቻሉ ፣ ይህ ራሱ አንድ ተአምር ነበር ።

በዘመናት መካከል ሰዎችበብዙ ጥረትና ትጋት ያስገኙአቸው ሥነ—ጽሑፎች በተዋቡና በከበሩ ቦታዎች በቤተ መጻሕፍት ወመዘክር ተከማችተው እነርሱን ለማየትና ለመመልከት ከመጣው ሁሉ ጋር በመተያየትና በመነጋገር ዕውቀትንና ትምህርትን በመስጠት ላይ ይገኛሉ ።

ስለዚህ በመጽሐፍ ያለ የሚወረስና ትምህርትም የሚሰጥ በቃል ያለ ደግሞ የሚረሳና የሚዘነጋ መሆኑ በዚህ ሊታወቅ ይችላል ። ይህም የስነ ጽሑፍን ጠቃሚነት በበለጠ ያስረዳል ።

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ክፍለ ዓለም በሰሜን ምሥራቅ አፍሪካ የምትገኝ ጥንታዊት ሀገር ስትሆን በተፈጥሮ አቀማመጥም «ቀርነ አፍሪካ» (የአፍሪካ ቀንድ) እየተባለች ትጠራለች ።

ኢትዮጵያ ጥንታዊ ሥልጣኔ ካላቸው ሀገሮች አንድዋ እንደመሆኗ በአውሮፓውያንም ሆነ በሌሎቹ ስነ—ጽሑፍ «ኢትዮጵያና አቢሲኒያ» በመባል የታወቀች ናት ።

«ኢትዮጵያ» የሚለው ስመ ተጸውዖ በመጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ቦታ ይገኛል ። በዕብራይስጡ ቋንቋ የተጻፈው መጽሐፍ ቅዱስ «ኢትዮጵያ» ለማለት «የኩሽ ሀገር» ሲል የዕርኡ ስነ—ጽሑፍ ደግሞ ኢትዮጵያ ይላል ። እንዲሁም በሮማንኛው የተጻፈው መጽሐፍ ቅዱስ «ኢትዮጵያ» ለማለት «ሳራ—ዴ—ኔግሪ» (በፀሐይ ግለት የተዋቡ ሰዎች ሀገር) ይላታል ። ሁለቱም ኢትዮጵያ ለማለት በተለያዩ የስነ ጽሑፍ ቃላት ለመጠቀም ቢሞክሩም ዓላማቸው እንደ ዕርዑ ኢትዮጵያ ለማለት መሆኑን ያስረዳል ።

ነቢዩ ዳዊት «ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር» (ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች) ይላል) መዝሙር ፷፯) በዚህና ይህን በመሳሰሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ስነ—ጽሑፎች ኢትዮጵያ «ሀገረ እግዚአብሔር» መሆኗን እንረዳለን።

በኢትዮጵያ የካህናት ከተማ ተብላ ትጠራ የነበረችው የአክሱም ከተማ ስነ ጽሑፍ በዘመኗ የትምህርት ዓለም ከተባለችው ከአቴና ከተማ ስነ ጽሑፍ ጋር የሚወዳደር እንደነበር ታሪክ ይነግረናል ። የኢትዮጵያ እምነትና ታሪክ ስነ ጽሑፍ ፣ ቋንቋ ፣ ባህል በጠቅላላው ኪነ ጥበብ ኢትዮጵያ በቀይ ባሕርና በሜዲትራኒያን ባሕር አካባቢ በነበሩትና ባሉት ሀገሮች ከነበራት የቀረበ ግንኙነት የተገኘ ፣ በነዚህም ሀገሮች የእምነት ሥልጣኔ የበለጸገች በቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት የታረቀች የራስዋን ፊደልና ቋንቋ በጠቅላላውም የራስዋን ኪነ ጥበብ አክብራ፣የስነ ጽሑፍን ሥነ ሥርዓት ጠብቃ ፣ እምነቷን አጽንታ የያዘች አንዲት በተራራ ላይ የታነጸች መሰወር የማትችል ታሪካዊት ከተማ ናት ።

በኢትዮጵያ እስከ ሃያኛው ምእት ዓመት መጀመሪያ ድረስ ስነ—ጽሑፍና ትምህርት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሀዶ ቤተ ክርስቲያን ቁጥጥር የተወሰነ ሁኖ ብዙ ዘመናት አልፈዋል ። በኢትዮጵያ የትምህርትና ስነ—ጥበብ ባለቤት የነበረችው የሆነችውም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከሌሎች ስነ—ጽሑፍን ሳትቀላውጥ የራሷ የስነ ጽሑፍና የአመራር አቋም በራሷ ሊታውንት እንደተጠበቀ ለረጅም ዘመናት መቆየቱ ግልጽ ነው ። በሥርዓተ ቅዳሴዋ እንኳን ከጥቂቶቹ የግሪክኛ ቃላት በቀር የቅብጥ ወይንም የዓረብኛ አንድ ቃልም ቢሆን ተለጥፎ አይገኝም ።

በተለያዩ ምክንያቶች በዘመን ብዛት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከጊዜ በፊትም ሆነ ከጊዜ በኋላ የሚጠበቅባትን ያህል የሥነ ጽሑፍ ዕድገት ከመገንባት ወደ ኋላ ያለችበት ጊዜ ባለመኖሩ በኢትዮጵያ የትምህርትና ስነ ጽሑፍ ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያውን ደረጃ የያዘች መሆኑ የማያጠራጥር ነው ። በኢትዮጵያ ትምህርትና ሥነ ጽሑፍ ተጀመረ ከተባለበት ዘመን አንስቶ እስከ ፲፱፻፲፩ ዓ.ም ድረስ በኢትዮጵያ የታወቀ የማተሚያ መሳሪያ ሳይኖር የኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ስነ ጽሑፋቸውንና ድርሰታቸውን የሚጽፉት በእጃቸው ብራና አውጥተው ቀለም አሽተው ፣ ብርዕ ቀርጸው ነበር አሁንም ይኸው ኢትዮጵያዊ የሥነ ጽሑፍ ጥበብ እየተሠራበት ይገኛል።

የኢትዮጵያ ገዳማት ከስድስተኛው መቶ ዘመን ጀምሮ እስከ አለንበት ዘመን ድረስ የስነ ጽሑፍ ፣ የታሪክ የማኅበራዊ ሕይወት ፣ የትምህርት በጠቅላላውም የኪነጥበብ መገኛዎች ሁነው መቆየታቸው በታሪክ የታወቀ ነው ። ቤተ ክርስቲያናችን በዘመናት መካከል ስለ ስነ ጽሑፍ እድገትና መስፋፋት ያደረገችው ጥረትና ትጋት በቀላሉ የሚገመት አይደለም። ቤተክርስቲያንናችን በግእዝ ቋንቋ በእጅ በብራና ላይ የተጻፉ እጅግ በጣም የሚያስደንቁ ወጣቱንም ሆነ አረጋውያንን የሚጠቅሙ የሃይማኖትና የስነ—ምግባር እንዲሁም መንፈሳዊውንና ሥጋዊውን ሕይወት የሚገልጹ ቁጥራቸው የበዛ መጻሕፍት አሏት ። ስለዚህ ቤተክርስቲያንናችን መሠረቱ የጸና የጐላ ለረጅም ዘመን የታሪክ ጉዞ ያለው ስነ—ጽሑፍ ያላት መሆኑ ግልጽ ነው። ይህም የስነ ጽሑፍ ክምችታችን ኢትዮጵያውያንን ብቻ ሳይሆን መላ አፍሪካን የሚያኮራ ዓለምንም የሚያስደንቅ ነው ። አፍሪካውያን የራሳቸው የሆነ ፊደልና የስነ—ጽሑፍ ደንብ አጥተው በሮማውያን ቋንቋ በላቲን ፊደልና የስነ ጽሑፍ ሕግ ሲጠቀሙ ይታያሉ ።

ለአፍሪካ ሕህጉር ታላቅ አገልግሎት ላበረከቱት ለሚስተር ሮበርት ኬ-ኤ ጋርድነር በ፳፮—፲—፲፱፻፷፬ ዓ-ም አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የክብር ዶክትሬት ሽልማት በተቀበሉበት ወቅት የተሰማቸውን ደስታ በመግለጽ ባደረጉት ንግግር «አንድ ዩኒቨርሲቲ በሞራል ዓላማ ላይ የተገነባ ለመሆኑ የጥንቶቹ የኤሮፓውያን ዩኒቨርሲቲዎች አቋም በገዳምና በልዩ ልዩ የመንፈሳዊ ትምህርት መስጫ ድርጅቶች ላይ የተመሠረተ ለመሆኑ ታሪክ ያስረዳልና ። አውሮፓውያን ይሠሩበት እንደ ነበረ ሁሉ ፣ ኢትዮጵያም በበኩሏ መሠረታዊውን የሀገር ትምህርት በገዳማት በልዩ ልዩ ሥፍራዎች በማስተማር ለዛሬው ዘመናዊ ዕውቀት መሠረት የሆነውን ትምህርት በግእዝ ቋንቋ ለማቆየት ችላለች ብለዋል ። እስከ ሃያኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ ገደማ ድረስ በኢትዮጵያ ትምህርትና ስነጽሑፍ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን መሪነት በሚዘጋጁ መጻሕፍት ለዛሬው ዘመናዊ ዕውቀት መነሻና መድረሻ በሆነው በመሠረታዊው የሀገር ትምህርትና ስነ—ጽሑፍ ራሷን በራሷ እያስተማረች ከዚህ አድርሳለች ።

ግእዝ የኢትዮጵያ ጥንታዊ የስነ ጽሑፍ ቋንቋ በመሆኑ ብዙ የታሪክና የስነ—ጥበብ መጻሕፍት የተጻፈበት እጅግ በጣም የዳበረና የታወቀ ነው። በአሁኑ ጊዜም በኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍ እያደገና እየዳበረ ሲመጣ በርካታ የግእዝ ቃላት ከቤተ ክርስቲያን የቃላት መዝገብ እየወጡ አገልግሎት በመስጠት ላይ ናቸው ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስነ—ጽሑፎችና የታሪክ ቅርሶች ምንም እንኳን አልፎ አልፎ በዘመናት መካከል በጠላት መበዝበዝና በእሳት ቃጠሎም መጋየት ቢደርስባቸውም ቅሉ ፣ እስከአሁንም ድረስ ቢሆን ቤተ ክርስቲያኒቱ የትምህርትና ስነ—ጽሑፍ በጠቅላላውም የኪነ ጥበብ መደብር ሁና መገኘቷ የታወቀ ነው ።

በዚህ ዓይነት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ከሠራዊተ ፊደል እስከ ቅዱሳት መጻሕፍት ስነ—ጽሑፍ ከዚህም ጋር ያለውን ሁሉ በመጻፍና በመጠበቅ ሀገርንና ወገንን አገልግላለች ። ከጊዜ በኋላም ጊዜውና አቅሟ በሚፈቅደው መሠረት ሁሉንም ማስተማር በሚለው መመሪያዋ አስተምራለች ።

ስለዚህ የኢትዮጵያን ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በዘመናት መካከል አገልግሎቷን ሳታቋርጥ መሠረታዊውን የሀገር ትምህርትና ስነ—ጽሑፍ ለረጅም ዘመናት በማስተማር ኅብረተሰቡን ያገለገለች ናት አሁንም በማገልገል ላይ ትገኛለች ።

የሀገሪቱ መንፈሳዊ ሕይወት ፣ አንድነትና ነፃነት ፣ ታሪክ ፣ እምነት ፣ ባህልና ሥነ—ሥርዓት እነዚህንም የመሳሰሉት ሁሉ ለብዙ ዘመናት ተጠብቀው የኖሩት በዚች እናት ቤተ ክርስቲያን ብርታትና ጥረት ነው ።

ቤተ ክርስቲያናችን በስነ—ጽሑፍ ሥራ በዓለም እጅግ በጣም የሚያስደንቁና ተወዳዳሪ የማይገኙላቸው በቤተ ክርስቲያናችን ቋንቋ በግዕዝ የተጻፉ ብዙ መጻሕፍት አሏት ብለናል ። እነዚህንም ያልተተረጐሙትን መጻሕፍት ወደ ሕዝብ ቋንቋ ተርጉሞ ምእመናን አንብበው እንዲረዱ በማድረግ አሁንም ቤተ ክርስቲያናችን ከፍተኛ ኃላፊነት አለባት ።

ለዚህም የስነ—ጽሑፍ ሥራ የሃያ ዓመታት የሥራ ልምድ ዕውቀትና ችሎታ ያለው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት ስለሆነ ፣ እስከ አሁን ቅዱሳት መጻሕፍትን በመተርጐም ፣ በስነ ጽሑፍ ሥራ ፣ በስብከተ ወንጌልና በሌላውም ለቤተክርስቲያን ፣ ለሀገርና ለወገን ያበረከተው አገልግሎት ከፍተኛና ጠቃሚ በመሆኑ ባለፉት ሃያ ዓመታት እንዳደረገው ሁሉ ባለፈው የሥራ ልምድና ችሎታ በመጠቀም ወደፊትም የስነ—ጽሑፍ ሥራውን በበለጠ እንደሚቀጥል ተስፋ እናደርጋለን ።

## የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ...

ከ፲፬ኛው ገጽ የዞረ

ውን በቅንነትናበታማኝነት እንዲያገለግል ሆኖ ሲዘጋጅ የቆየ ነው ።

፮- የደኅንነት ቀን

ይህ ፕሮግራም በክርስቶስ መንገድ ለመሄድ ማመን የሚያስፈልገውትናንት ወይም ነገ ሳይሆን ፤ ዛሬመሆኑን ማንኛውም ክርስቲያን አምኖ በአለበት ቅፅበት ማመንና መልካምሥራ መሥራት እንዳለበት የሚያስገነዝብ ዝግጅት ነበር ።

፯- ክርቲያናዊ ሕይወት (ሃይማኖትነክ)

ይህ ፕሮግራም እውነተኛ ክርስቲያናዊ ጠባይና አኗኗር እንዴት እንደሚሆንና መሆን እንደሚገባ የሚያስተምር ዓላማ ነበረው ።

፰- ሴቶች በማኅበራዊ ኑሮ ፤

ይህ ፕሮግራም ልማት ነክ ሲሆን በማንኛውም ማኅበራዊ ኑሮ ማለት እንደትምህርት ፤ እንደ ሕክምና፤እንደ ጤንነት ፤እርሻ በመሳሰሉት በማንኛውም ጥበበ ዕድ ሴቶች ያላቸውን ተሳትፎ የሚገለጽበት ነው ።





www.ethiopianorthodox.org

፱- <u>ግእዝ በራዲዮ ፤</u>

( የልማት ፕሮግራም )

የኢትዮጵያ ጥንታዊ ቋንቋ የሆነውን ግእዝ ለመማር የሚፈልጉትን ሰዎች እንዲማሩ የሚረዳ ዝግጅት ነው ።

፲-መዝሙር (የመዝናኛ ፕሮግራም )

ለአድማጮች ልዩ ልዩ መንፈሳዊ መዝሙሮችን ማሰማትና የአድማጮችን ፍላጐት ማርካት ነበር ።

፲፩- <u>የኢትዮጵያ ቅኔዎች</u>

(የመዝናኛ ፕሮግራም )

ቢታወቁ ሊቃውንት በኢትዮጵያ ባሉት ቋንቋዎች ካሁን ቀደም የተነገሩትን ቅኔዎች ከነፍቻቸው ማስጠናትና አድማጨንምይህን የመሰለውን ትምህርት እንዲያውቅለማድረግነው።

፲፪ <u>ለኑሮህ ምን ትሠራለህ?</u>

(የልማት ፕሮግራም )

ሥራ የሰው ልጆች በረከት እንጂ እርግማን አለመሆኑን አምኖ በአልጋ ቁራኛ ፤ በደዌ ዳኛ ከተያዙት በሽተኞችና ሕመምተኞች በቀር ማንኛውም ሰው የሥራን ክቡርነት አውቆ በችሎታው ወደሥራ እንዲሠማራ የሚገፋፋ ዝግጅት ይገኝበት ነበር ።

፲፫- <u>«የተጻፈው ሁሉ ለኛ ተጻፈ »</u>

( ሃይማኖት ነክ ዝግጅት )

በዚህ ፕሮግራም አድማጮች የሚረኩበት መንገድ እየታቀደ በልዩ ልዩ ሊቃውንት የተዘጋጁ መጻሕፍትን በማንበብ የሚያሳውቅ ፕሮግራም ነበር ።

፲፬- <u>ቤተ ክርስቲያን በማኅበራዊ ኑሮ</u> (ታሪክ ነክ ፕሮግራም)

ይህ ዝግጅት ይቀርብ የነበረውቤተ ክርስቲያን በትምህርት ቤቶች በጤንነት በሰበካ ጉባኤ በልማት እየገባች የምታስተምረውን ተሳታፊነት የሚገልጽ ሆኖ ነው ።

፲፭- <u>አካባቢና ጤንነት</u>

( የሰዎች ግዳጅ )

ሰዎች ጤንነታቸውን እንዲጠብቁ ከዚያም አልፈው የአካባቢያቸውን ፅዳት እንዴት አድርገው መጠበቅ እንዳለባቸው የሚያሳውቅ ፕሮግራም ነበር ።

፲፮- <u>ኑሮ በከተማ (ልማት )</u>

ይህ ዝግጅት በከተማ የሚኖረውን ሕዝብ ሁሉ እየጠየቀ ምን ችግር እንዳለበትና ችግሩን ለሚመለከተው ክፍል በመጠቆም ደኅንነት እንዲያገኝና የከተማው ሕይወት የሚጠበቅበትን የሚጠቁም ነው ።

፲፯- <u>ትምህርታዊ ዕድገት(ልማት )</u>

ትምህርት ከምን እንሥቶ ከምን እንደደረሰ ተንትኖ ማስረዳት ፤ እንዲሁም በተለይ የሀገራችንን ትምህርት ከዘመኑ ትምህርት ጋር በማዛመድ ለአድማጮች የሚያቀርብ ፕሮግራም ነበር ።

፲፰- <u>ኑሮ በገጠር ( ልማት )</u>

በገጠር የሚኖሩት ነጋዴዎች ገበሬዎች አስተማሪዎችና ልዩ ልዩ ግለሰቦች ኑሮአቸውን የሚያሻሽሉበትን መንገድ የሚጠቁም ዝግጅት ነው ።

፲፱- <u>ወጣቶችና ዓላማቸው</u>

( ሃይማኖት ነክ )

ይህ ዝግጅት ወጣቶችን ከቤተ ክርስቲያን እንዳይርቁ የሚያስተምርና የሚስብ ከመሆኑም በላይ ወጣቶች ለቤተ ክርስቲያን ያላቸውን ዓላማና በማኅበራዊ ኑሮ ያላቸውን ተሳታፊነት በየጊዜው እየቀረቡ የሚገልጹበት ነው ።

፳- <u>የአድማጮች ጥያቄና መልስ</u>

( ል ማ ት )

የፕሮግራሙ ተከታታዮች ለሚያቀርቡዋቸው ጥያቄዎችና አስተያየቶች የመሳሰሉት ሁሉ ተገቢው መልስ እየተዘጋጀ የሚሰጥበት ክፍለ ጊዜ ነበር።

፳፩- <u>ሴቶች በጤንነትና በልጅ አስተዳደግ</u> (ል ማ ት)

ተተኪው ትውልድ በጤንነት ፤ በመልካም አስተዳደግ ፤ በትምህርት በልጽጎ እንዲያድግና ሀገሩንና ወገኑን እንዲያገለግል ለማዘጋጀት ታቅዶ የተያዘ ፕሮግራም ነው ።

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ፕሮግራሞች በአማርኛ ፤ በትግርኛ ፤ በኦሮምኛ ፤ በአጠቃላይ የራዲዮ ፕሮግራሙን እስከ አቋረጠበት ጊዜ ድረስ ከ፶፮—፷፯ ፣ የ፩ሺ ፩፻፰ ሰዓታት ከ፷፯—፰፱ የ፩ሺ፶፭ ሰዓታት በድምሩ የ፪ሺ፷፻፲፭ ሰዓታት ትምህርት አስተላልፎአል ።

<u>የሥነ ጽሑፍ ክፍል የሥራ ዕድገት</u>

የምእመናን መንፈሳዊ ፍላጐት እያደገ የአንባብያንም ቁጥር እየበረከተ በመሄዱ ድርጅቱ «ድምፀ ተዋሕዶ ጋዜጣ» ቀድሞ ከነበረው መጠን ከፍ ብሎና ብዛቱም ጨምሮ እንዲወጣ ባለው ዕቅድ መሠረት « ድምፀ ተዋሕዶ ጋዜጣ » ከግንቦት ወር ፲፱፻፷፰ ዓ. ም. እስከ ጥር ፲፭ ቀን ፲፱፻፸፩ ዓ.ም. ድረስ በወር አንድ ጊዜ ሲያሳትም ቆይቶአል ።

ጥቅምት ፳፱ ቀን ፲፱፻፸፩ ዓ. ም. ድርጅቱ አጠቃላይ ስብሰባ አድርጐ

## ሀ· <u>ድምፀ ተዋሕዶ ጋዜጣ</u>

በወር አንድ ጊዜ መሆኑ ቀርቶ የምእናንን ፍላጐት ለማርካት ጥያቄአቸውንም ለማሟላት ሲባል በየአሥራ አምስቱ ቀን ብዛቱን በከፍተኛ ደረጃ ጨምሮ እንዲታተም በወሰነውመሠረት ከጥር ፴ ቀን ፲፱፻፸፩ ዓ.ም. ከቁጥር ፩፻፹—፪፻፷፫ መስከረም ወር ፲፱፻፸፭ ዓ. ም. መጀመሪያ ድረስ በ፩፻፴፫ ርእሶች ፬መቶ፳፮ ሺህ (አራት መቶ ሃያ ስድስት ሺህ ኮፒዎች ታትመው ለምዕመናን ተዳርሰዋል ።

## ለ· <u>ትንሣኤ መጽሔት</u>

ትንሣኤ መጽሔት ከቁጥር ፱ ጀምሮ የሥራው ጥራትና ይዘት የጽሑፉ ተፈላጊነት ለዘመኑ በሚስማማና የእምነት ትምህርት የሚናፍቃቸውንና እምነታቸውን ለማጠንከር



ለሚፈልጉ ሁሉ በበሰሉ ሊቃውንት ነገረ መለኮት ጭምር እየተዘጋጀ እንዲሰጥ በተወሰነው መሠረት ከመስከረም ወር ፲፱፻፸ ዓ. ም. እስከጥር ወር ፲፱፻፸፩ ዓ. ም. ድረስ በየሁለቱ ወር ሲታተም ከቆየ በኋላ መጽሔቱ በየወሩ እየታተመ እንዲቀርብ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ምዕመናን ጥያቄ ስለአቀረቡና የተለያዩ አስተያየቶችም በየቀኑ ይጐርፉ ስለነበረ ፤ የምዕመናንን ጥያቄ ለማሟላት ከጥር ወር ፲፱፻፸፩ ዓ. ም. ጀምሮ በየወሩ እንዲታተም ተደረገ ። የጽሑፉ ጥራትም በይበልጥ አምሮ እንዲቀርብ የሚያስፈልጉ ደራስያን ተጨምረው በማኅበራዊ ኑሮ በጤና አጠባበቅ በነገረመለኮት ፤ በግዕዝ ትምህርት በታሪክ ፤እንዲሁም ምርምራዊ የሆኑ ጽሑፎችን በማቅረብ ፤ አስደናቂ ነገሮችን በመከታተል ተአምራዊ ዜናዎችን የሊቃውንት ታሪኮችን በማቀናበር በአጠቃላይ እስከ ፲፱፻፸፭ ዓ. ም. መጀመሪያ ድረስ በ፭ ዓመታት ውስጥ ፩ሺ፩፻፹፫ ርእሶችን ጽፎ በብር ፩ አሳትሞ በ፶ ሣንቲም ፪፻፸፭ሺ፩፻፶፬ ኮፒዎችን ለምዕመናን አዳርሶአል ።



በአሁኑ ጊዜ ካሉት የድርጅቱ ሠራተኞች በከፊል

## የተዘዋዋሪ ሥነ ምግባር <u>ሰብከተ ወንጌል ክፍል</u>

ሀ/ ይህ ቡድን ለትምህርተ ወንጌል አመቺ በሆኑ በኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገርና በአዲስ አበባ ሁሉ እየተዘዋወረ ለማኅበራዊ ኑሮ የሚያስፈልጉትን ትምህርቶች እያስተማረ ሕዝቡ የራሱን ችግር ራሱ በመረዳት ለችግሩ መፍትሔ እንዲያገኝ መንፈሳዊ ቅስቀሳና ትምህርት በመኪኖች ባሉ ድምፅ ማጉያዎች አማካይነት የሚያደርስ ነው ።

ለ/ በኢትዮጵያ ብዙ መንፈሳውያን የቤተ ክርስቲያን በዓላትአሉ ። በነዚህም የበዓላት ቀን ከአርባ ሺህ እስከ ሃምሳ ሺህ የሚሆኑ ምዕመናን ይሰበሰባሉ ። ድርጅቱ የስብከተ ወንጌልናተዘዋዋሪ ሰባክያንን በመመደብ የወንጌል ትምህርትን ለማኅበራዊ ጉዳይ ጠቃሚ የሚሆኑትን ስለጤና ፤ ስለግብረ ገብ ፤ ስለሥራ ክቡርነት ፤ ስለነገረ መለኮት፤ ስለትምህርታዊዕድገት በአጠቃላይ ሰዎች የራሳቸውን ችግር ራሳቸው መፍትሔ እንዲፈልጉና እንዲያስወግዱ አጠቃላይጠቃሚ ትምህርት ይሰጣል ።

ሐ/ በእሑድ ትምህርት ቤቶች በየሳምንቱ የሰንበት ትምህርት በሚሰጥባቸው ቦታዎችና መንፈሳዊ ማኅበሮች ካሉባቸው ቦታዎች እየተዘዋወረ ያስተምራል ።

መ/ በጠባይ ማረሚያና በወህኒ ቤቶች እየሄደ ለወጣቶች የሞራልና የግብረ ገብ ትምህርት ለእስረኞችም ካለባቸው ጠባይ—ተላቀው ወደማኅበራዊ—ኑሮበሚመለሱጊዜ ከኅብረተሰቡ ጋር መኖር እንዴት እንደሚችሉና ያለባቸውንም ስሕተት ሁሉ አምነው ራሳቸውን በራሳቸው መክረው ለኅብረተሰቡ ጠንቅ የሆኑትን ነገሮች አስወግደው በመልካም አኗኗር እንዲኖሩ (የሞራል) የሥነ ምግባር ትምህርት የሚሰጥ ክፍል ነው ።

ከዚህም በቀር ከ፲፱፻፷፪ ዓ.ም. ጀምሮ በከፋ ክፍለ ሀገር በማጂ አውራጃ ጨብራ እየተባለ በሚጠራው ቦታ አንድ ተዘዋዋሪ ሰባኬ ወንጌል መድቦ የግብረ ገብና መንፈሳዊ ስብከት እንዲያስተምር አድርጐ በማስተማር ላይ ገኛል ።

በዚህም መሠረት ከ፲፱፻፶፮ ዓ.ም. እስከ ፲፱፻፷፰ ዓ. ም. ድረስ በአዲስ አበባና በአሥራ አራቱም ክፍላተ ሀገር በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ምእመናንን አስተምሮዋል ። በዚህም ከብዙ ሺህ ምእመናን አስተያየት ምስጋናና ሽልማትም አግኝቶአል ።



www.ethiopianorthodox.org

ከ፲፱፻፷፰ ዓ. ም. እስከ ፲፱፻፸፬ ተዘዋዋሪና የሥነ ምግባር ቡድን

ቤተ ክርስቲያን ሥራ በመፍጠር የድርጅቱን ሠራተኞች እንድታሠራ በመንግሥት ስለተፈቀደ ፤ ድርጅቱም አዲስ ሥራ በመፍጠር የነበረውንም ሥራውን አሻሽሎ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን በይበልጥ ለማገልገል የምእመናንንም ፍላጎት ለማርካት በአዲስ ዕቅድ ተነሣሥቶ በአራት ኮሚቴዎች ሥራውን ከፍሎ እስከ አሁን ድረስ በትጋትና በቅልጥፍና በመሥራት የምእመናንን ፍላጎት ለማርካት ይጥራል ።

እነዚህም ኮሚቴዎች ፩ኛ ሥነ ጽሑፍ ፪ኛ ተዘዋዋሪ ጓድ ፫ኛ የማከፋፈያ ኮሚቴ ናቸው ።

በአራት ከተከፈሉት ኮሚቴዎችም አንዱ የተዘዋዋሪ ሥነ ምግባር ቡድን ነው ይህ ቡድን ከ፲፱፻፷፰—፲፱፻፸፬ ዓ.ም. መጨረሻ ድረስ በመላዋ ኢትዮጵያ በሚገኙት ክፍላተ ሀገር በታላላቅ በዓላት ጥራት ያላቸው የወንጌል መምህራንን እየላከ ለምእመናንስብከተ ወንጌልን በማስተማር ጋዜጦችና መጽሔቶችም እግረ መንገዱን በማዳረስ በጥቂት ጊዜ ውስጥ በጠቅላላው በ፰ ዓመት ውስጥ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ምእመናንን ለማስተማር በመብቃቱ ድርጅቱ ባከናወናቸው ሥራዎች ቤተ ክርስቲያን ትኮራበታለች ።

## የውጭ ግንኙነት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት ከሀገርም ሆነከልዩ ልዩ የውጭ ሀገር ድርጅቶች ጋር ባለው ጠንካራ ግንኙነት መሠረት ከፈጸማቸውም ተግባራት ወደሩማንያ ፤ ግሪክ እንግሊዝ አሜሪካ ፤ ኬንያ ፤ ዛምቢያ ፤ ም ሑራንን በመላክ ወደ ፴ የሚደርሱ ኢትዮጵያውያን በልዩ ልዩ ሙያ ሠልጥነው ወደሀገራቸው በመመለስ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናቸውን ሲያገለግሉ ከመቆየታቸውም ሌላ ፡ አሁንም ለኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ እጅግ ጠቃሚ የሆኑ ሊቃውንትን ማፍራት ተችሎአል ።

ከነዚህም በአገር ውስጥ በከፍተኛ ሥልጣን ላይ ሆነው ለኢትዮጵያ ቅን አገልግሎት በማበርከት ላይ ከመሆናቸውም በላይ በአገር ውጭም በአምባሳደርነት ኢትዮጵያን በማገልገል ላይ የሚገኙት በቂ ማስረጃዎች ናቸው ።

ዛሬም በዚሁ ጠንካራ ግንኙነት መሠረት ወደተለያዩ አገሮች ደቀመዛሙርትን እየላከ ድርጅቱ በማስተማር ላይ ይገኛል ። በማንኛዎቹም ዓለም አቀፍ መንፈሳውያን ስብሰባዎች ድርጅቱ ተካፋይ በመሆኑ ፤ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ፤ በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ና በሌሎችም ድርጅቶች በሚሠራው የመገናኛ ዘዴዎችና የማሠራጫና ማደራጃ (ሚዲያ አገልግሎት ) ታውቆ የተመዘገበበመሆኑ ለሌሎቹ የሚደረገው ዓለም አቀፍ ርዳታ ሁሉ ለድርጅቱም ይደረግለታል ።

የዓለም ሉተራውያን ፌዴሬሽን በዓለም ላሉት እስቱዲዮች ለፕሮግራም ማስፋፊያ ሲፈቅድ ድርጅቱም ከዓለም መንፈሳዊ መገናኛ ( ሚዲያ ሴንተር) ጋር ባለው ግንኙነት መሠረት ለድርጅቱ ፕሮግራም ማስፋፊያናማሻሻያ እንዲሁም ለልማት ፕሮግራም አገልግሎት የሚውል ድርጅቱ በሚያቀርበው ፕሮጀክት መሠረት ፤ ከ፲፱፻፷፬ ዓ. ም. ጀምሮ እስከአሁን ድረስ ርዳታ ለማግኘት ችሎአል ።

በየዓመቱም ለድርጅቱ የሚሰጠው የዕርዳታ ገንዘብ የዕርዳታ ሰጭው ድርጅት እንስፔክተሮች ሥራውንና ሁኔታውን እየተቆጣጠሩ ለዓለም ሉተራውያን ፌዴሬሽን ሪፖርትሲያቀርቡ ድርጅቱ እንደገና ፕሮጀክት እያቀረበ ሌላ በጀት በማግኘት ቆይቶአል ። ወደፊትም የድርጅቱ ርዳታ በዚሁ ዓይነት ቀጥሎ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የምትፈቅደውን አገልግሎት ለማበርከት የበለጠ ዝግጅት ያደርጋል ።

## መንፈሳዊ ኮርስ

ኮርስ ማለት ለብዙ ጊዜ የተደከመበትን መጠነኛም ሆነ ሰፊ ትምህርት በሥራ ላይ ለማዋል የሚቻልበትን ዘዴ ለማወቅ በተወሰነ ጊዜ ለተወሰኑ ሰዎች በተወሰኑ መምህራን ተነጥሮና ተጨምቆ ልዩ የማሠልጠኛ ትምህርት የሚሰጥበት ጥበብ ነው ።

የዘመኑ ሥልጣኔ ዕድገት በተለያዩ ዕቅድ እየተለዋወጠ እንደመሄዱ መጠን፤ የሰዎችም አእምሮ በየጊዜው የመጥበብም ሆነ የመስፋፋት ጠባይ አለው ። ለዚህም መመዘኛውና መለኪያው በየጊዜው የሚሰጥ የኮርስትምህርት ነው ።

ታዲያ በዚሁ ጥበብ ለመጠቀም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶሐዋርያዊ ድርጅት ካህናትን የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን በኮርስ አሠልጥኖ ችሎታቸውን አሻሽለው ቅድስት ቤተ ክርስቲያንንና ምዕመናንን በቅን እንዲያገግሉ አድርጐአል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የመገናኛ ማደራጃና ማሠራጫ (ሚዲያሴንተር) አባል በመሆን በየክፍላተ ሀገሩ የሚገኙትን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተወካዮች በየዓመቱ የክረምት ወራት የ፵፮ ቀኖች ኮርስ በማዘጋጀት በሺህ የሚቆጠሩ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ካህናትን ለሥራ ለማዘጋጀት ከመብቃቱም በላይ እንዲሁም በውጭ አገር በየጊዜው በሚዘጋጁት ኮርሶች ድርጅቱ የራሱንደራ

ተከታዩ በ፳፯ኛው ገጽ ይገኛል

# አዲስ ዓመት

ከሐዲስ ተረፈ ፤

ይህ ርእስ በስድስት ሆኅያት በሁለት ቃላት የተቀነባበረ ነው ። በቅድሚያ ለጽሑፋችን መነሻ ለሐሳባችን ማጉልመሻ ይሆን ዘንድ አዲስና ዓመት የሚሉት ሁለት ቃላት በተናጠል ምን እንደሆኑ እንመልከታቸው ።

አዲስ የሚለው ቃል ሁልጊዜለሰው አእምሮ ይስማማል ፤ለጆሮ ይጥማል ፤ ዓይንን ይማርካል ። ስለዚህ ሰዎች አዲስ የሚለውን ገላጭ ቅጽል ከአያሌ ነገሮች ጋር አዛምደው ሲጠቀሙበት እናያለን ። ከብዙ በጥቂቱ ለመጥቀስ ያህል ፤ አዲስ ነገር አዲስ ትምህርት ፤ አዲስ ሐሳብ ፤ አዲስ ሕይወት አዲስ መንፈስ ፤ አዲስ ቋንቋ ፤ አዲስ ሥርዓት ፤ አዲስ ትውልድ ፤ አዲስ ልብስ ወዘተ እየተባለ ደስ ለሚል ነገር ሁሉ መግለጫ ሲሆን እናገኘዋለን ። ቱሪስቶች ባሕር አቋርጠው ፤ ተራራ ዞረው ፤ ገንዘባቸውን ከስክሰው ፤ ዓለምን የሚዞሩት አዲስ ነገር ለማየት ነው ። ልጅ አዲስ ልብስ በተገዛለት ቀን ቁመት ጨምሮ ያድራል የሚለው ባህላዊ አነጋገር አዲስ የሚለው ቃል ምን ያህል ክብደት እንዳለው ይገልጻል ።

ቤተ ክርስቲያን አዲስ የሚለውን ቃል ከፍተኛ ትርጉም ሰጥታ ስትገለገልበት እናያለን ። ከወንጌለ ማቴዎስ እስከ ራዕየ ዮሐንስ ያሉትን ሃያ ሰባት መጻሕፍት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ምሥጢረ ልደት ምክንያት ሰውና እግዚአብሔር የታረቁበትን ፤ በምሥጢረ ትንሣኤው ዘለዓለማዊ ሕይወት የተገኘበትን የምሥራች ስለሚያበሥሩና በጠቅላላው ለክርስትና እምነት መራኁት ስለሆኑ ፤ ሐዲስ ኪዳን ብላ ሰይማቸዋለች ። እንዲሁም እነዚህ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ፤ ትውፊትን መሠረት በማድረግ ብጥር ንጥር ብሎ ጥልቀትና ምጥቀት ባለው በአንድምታ ትርጓሜ የሚተነተኑበት ትምህርት በቤተ ክርስቲያን ቋንቋ ትርጓሜ ሐዲስ እየተባለ ይጠራል ። ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ወዲህ ያለውን ዘመን ክርስቲያኖች ምሕረትን ፤ ነፃነትን ፤ ድኅነትን ያገኙበት ጊዜ በመሆኑ ቤተ ክርስቲያን «ዘመነ ሐዲስ» ብላ ትጠራዋለች ።

አዲስ የሚለውን ቃል ከዚህም በበለጠ መተንተን ይቻላል ። ሆኖ ም ብዙ ቢያወጡ ይዘነጉ ነውና ዓመት ወደሚለው ቃል እንዛወር ።

በአቡሻክር ቀመረ ትንታኔ አንድ ዓመት ሠላሳ አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሠላሳ ስድስት ሽህ ሰኮንድ ፤ አምስት መቶ ሐያ አምስት ሽህ ስድስት መቶ ደቂቃ ፤ ስምንት ሽህ ሰባት መቶ ስድሳ ሰዓት ፤ ሦስት መቶ ስድሳ አምስት ቀናት ፤ ከስድስት ሰዓታት ሃምሳ ሁለት ሳምንታት ፤ እንደኢትዮጵያ አቆጣጠር አሥራ ሦስት ወራት በውስጡ የያዘ ነው ። ለአቆጣጠር ያመች ዘንድ ይህ ሁሉ እልፍ አእላፍ አኃዝ ተጣፍቶና ተደምሮ አንድ ዓመት ይባላል ።

እንግዲህ ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርነው የሁለቱን ቃላት ገጽታ ከተገነዘብን አዲስ ዓመት ወደሚለውርእሳችን እንገባለን ። አዲስ ዓመት የሚባለው መሬት ምሕዋረ ፀሐይን በመከተል በሦስት መቶ ስድሳ አምስት ቀናት ውስጥ ፀሐይን አንድ ጊዜ ዙራ ከጨረሰች በኋላ ሁለተኛውን ዙር የምትጀምርበት ወቅት ነው ።

የአዲስ ዓመት መባቻ በተለያዩሀገሮች በተለያየ ሁኔታ ይከበራል ።

አውሮፓውያን አዲሱን ዓመት የሚጀምሩት እንደ አህጉራቸው ዘመን አቆጣጠር ጥር አንድ ቀን ክረምት ሲገባ ነው ። ብዙውን ጊዜ አዲስ ዓመት በሚከበርበት ዕለት የአየሩ ቅዝቃዜ ከዜሮ ዲግሪ በታች በጣም ዝቅ ብሎ ምድሩ በበረዶ ፤ ሰማዩ በደመና ተሸፍኖ ፤ ከጨለማው ብዛት የተነሣ ሌትና ቀኑን መለየት እስከሚያቅት ድረስ የፀሐይ ምልክት ሳይታይ ይውላል ። ይህን ዕለት ሁሉም ደረጃው በሚፈቅድለት መጠን ከቤቱ ሳይወጣ ሞቅ ያለ እሳት አንድዶ እየሞቀ በመብልና በመጠጥ ያሳልፈዋል ።

እንደ ባሕረ ሐሳቡ አቆጣጠር በሀገራችን አዲስ ዓመት የሚብተውመስከረም አንድ ቀን ነው ። መስከረም በሰኔ ተግብ ፤ በሐምሌ ጭፍና በነሐሴ እኝኝታ በዳጡ በማጡ ፤ በጭቃው ፤ በወልቁ ተመርሮና ተኮማትሮ የከረመውን ሰው በጳጉሜን አስተናጋጅነት የአሮጌውን ዘመን ጉዞ ጨርሶ ወደ አዲስ ዓመት በሚሸጋገርበት ወቅት ምድርን በልምላሜ ጉዝጉዞ ሜዳዎችንና ኮረብታዎችን ያሸበረቁ አበባዎች አልብሶ እንኳን ደኅና መጣህ በማለት ይቀበለዋል ።

የአዲስ ዓመት መባቻ ከታላላቅ የሕዝብ በዓላት አንዱ ስለሆነ በልዩ ዝግጅት ይከበራል ። አዲስ ዓመት በመጣ ቁጥር ታላላቅ ሱቆች ደንበኞቻቸውን ለማስደሰት የዋጋ ቅናሽ ያደርጋሉ ። እንኳን አደረሳችሁ በማለት ያሸበረቁ ጽሑፎች በበሮቻቸውና በመስኮቶቻቸው ላይ ይለጥፋሉ ። የኪነት ባለሙያዎች ዓመት ሙሉ የደከሙበትን የሙዚቃ ዝግጅት ለአዲሱ ዓመት አቅርበው ሕዝብን ይጋብዛሉ ። አዲሱን ዓመት ምክንያት በማድረግ መንግሥት በእመክሮ ላይ ለሚገኙ የሕግ እሥረኞች ምሕረት ሲያደርግ እናያለን ።

አዲሱን ዓመት በየመንደሩ ያሉወንዶች ሕፃናት «ሆያ ሆዬ»እየተጫወቱ ፤ ሴቶች ደናግል «አበባዩ ሆይ አደይ አበባ አደይ የብር ሙዳይ» የሚለውን ባህላዊ መዝሙር በየቤቱ እየዞሩ በመዘመር በደስታና በእልልታ ይቀበሉታል ። እያንዳንዱ ቤተሰብ የበዓሉ ዋዜማ ዕለት ችቦ በማብራት ጨለማ ወጣ ፤ ብርሃን መጣ ፤ አሮጌው ዓመት



www.ethiopianorthodox.org

አበቃ ፤ አዲስ ዓመት ተተካ በማለት አዲሱን ዘመን በአዲስ ሕይወት ፤ በአዲስ ተስፋ ለመቀበል ያለውን ምኞት በየቀዬው ሲወያይ ያመሻል ፤ዓውደ ዓመቱም ቂጠማው ቱጉዝጉዝ እርድ ታርዶ ፤ ዳቦ ተቆርሶ ይከበራል ። እንኳን አደረሳችሁ በመባባል ወዳጅ ዘመድ እርስ በርስ ሲጠያየቅ ይውላል ።

ወፍ እንደአገሯ ትጮሃለች እንዲሉ ሳይበዛ ፤ ሳይንዛዛ አካባቢው በሚፈቅደው ባህል ዓውደ ዓመቱን ማክበር ለሰውነት ዕረፍትን ፤ ለአእምሮ መዝናናትን ስለሚሰጥ ጉዳት ያለው አይመስልም ።

የዚህ ጽሑፍ ዓቢይ መልእክት የዘመን መለወጫን በዓል አፈ.አዊ ገጽታ ለመተረክ አይደለም ። እያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡር ውስጣዊ ሕሊናውን መርምሮ ፊት ለፊቱ በተዘረጋው የአዲስ ዓመት ሠሌዳ ላይ ምን መጻፍ እንዳለበት ለማስገንዘብ ነው ።ዘመንና ወራጅ ውሃ አንድ ጊዜ ካለፉ ተመልሰው አይመጡም ። ማስረጃ ካስፈለገ አጭር ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል ። ውሃ የሞላበት አዝማሪ ሙዚቃውን ሰምቶ ውሃው እንዲቆምለት ከወንዝ ዳር ቆሞ መሰንቆውን እየደረደረ እሸሸ ገዳሜ ቢል የሰማው ሲሄዶ ያልሰማው ስለሚመጣ ዓላማው ሳይሳካለት ቀረ ይባላል ።

ዘመንም እንደዚሁ ነው ለብዙዎቻችን በያመቱ የወራቶቹ ስም ስለማይለዋወጥ ያምናው መስከረምና የዘንድሮው መስከረም አንድ ዓይነት ይመስለን ይሆናል ። ይህን የምንል ካለን ተሣሥተናል ። አምናና ዘንድሮ የተለየ ባሕርይ ፤ የተለየ ጠባይ አላቸው የያንዳንዳችንን ሕይወት እንኳ ብንወስድ ከአምና ዘንድሮ ከተመደበልን ዕድሜ በአንድ ዓመት ቀንሰናል ። ታዲያ ዕድሜአችን እየቀነሰ ዘመኑ ዕረፍታችን እየተዳረሰ በሂደቱ ቁጥር ምን ሠራሁ?የሚለው ጥያቄ ሊደቀንብን ያስፈልጋል ። አምና እንዴት አለፈ? ዓላማ ኑሮናል ? ከዓላማችንስ ንቱን እጅ ተግባራዊ አደረግነው ? ያልተሳካልን ነገር ምንድን ነው ?እንቅፋቶቹስ ምን ነበሩ ? ዘንድሮስ ምን ዕቅድ አለን ? ።

በአሁኑ ጊዜ ለሥራም ሆነ ለትምህርት ከአንዱ ወደ ሌላው አገር የሚዘዋወሩ ሰዎች ካሉበት አገር ያለውን በሽታ ይዘው ለሌሎች እንዳያጋቡ ጉዞ ከመጀመራቸው በፊት በቅድሚያ መከተብ እንዳለባቸው ዓለም አቀፍ ሕግ ያስገድዳል ። በዚህ አንፃር በአዲስ ዓመት አዲስ ሕይወት ለመጀመር ከአሮጌው ዓመት የወረስነውን ጉስቁልና ፤ ሐኬትና ክፋት እንደዕባብ ገላ አውልቀን መጣል ይኖርብናል ።

ይህን በሚመለከት ጉዳይ ከክርስቶስ ልደት ሰባት መቶ ዓመት ቀደም ብሎ የተነሣው ነቢዩ ሕዝቅኤል በምዕራፍ ፲፰ ቁ-፴፩ ላይ « የበደላችሁትን በደል ሁሉ ከናንተ ጣሉ አዲስ ልብስ ፤ አዲስ መንፈስም ለናንተ አድርጉ» ይላል ። ይህ መልእክት ከጥንት ጀምሮ የሰዎች ልቡና በበደል ፤በተንኮል ፤ በቂም በበቀል የተሞላ መሆኑን ሲጠቁም አዲስ ሕይወት ለመጀመር ከነዚያ ነገሮች ነፃ መሆን እንዳለብን በግልጽ ያስተምረናል ።

በመሠረቱ ያነጋገር ፈሊጥ እንጂ አዲስ ዓመት ራሱ አዲስ ነገር ይዞ አይመጣም ። አዲሱን ዓመት አዲስ የሚያደርገው ሰዎች ዘመኑ መዋዕላቸውን ለሰላም ለጋራ ብልጽግና ፤ ለዕውቀትና ለፍትሕ ርትዕ ሲያውሉ ብቻ ነው ። ምንም ሳንሠራ መስከረም በጠባ ቁጥር አዲስ ነገር እንደ አደይ አበባ ከምድር ይፈነዳል ብለን የምንጠብቅ ካለን የዋሆች ያሰኘናል ። በሰኔ ያልዘራ በኀዳር አያጭድምና ።

በሌላም በኩል አዲስ ዓመት የውድድር ሜዳ ነው ። የጥንት ተረትና ምሳሌ ኤሊና ጥንቸል የሩጫ ውድድር ጀመሩ ይላል ። ውድድሩ እንደተጀመረ ጥንቸል በኃይል ፈርጥጣ ኤሊን ብዙ ኪሎ ሜትር ቀድማት ከሄደች በኋላ ዘወርብላ ብታይ ኤሊ ሩጫው ከተጀመረበት ቦታ ምንም ያህል ፈቀቅ አላለችም ጥንቸልም መቼም ይህች ጐታታ አትቀድመኝም ። ከዚህ ዛፍ ሥር አረፍ ልበልና አንድ አፍታ ሩጫ ውድድሩን እጨርሳለሁ ብላ ከዛፍ ሥር ጋደም እንዳለች እንቅልፍ ይዟትጅው አለ ። ኤሊ ግን አቅሟ በሚፈቅድላት መጠን ሳታቋርጥ ሩጫዋን ስለቀጠለች የሩጫውን ውድድር አሸንፋ ገባች ይላል ።

ምሳሌው የያንዳንዳችን ሕይወት ይመለከታል ። የሩጫው ሜዳ በፊታችን የተንጣለለው አዲስ ዓመት ነው ። ተወዳዳሪዎቹ ሁላችንም ነን ። ከዚህ ላይ የምንማረው እንደ ጥንቸል ፈጣን ነን ብለን መዘናጋት ፤ እንደ ኤሊ ፤ ዳተኞች ነን ብለን ተስፋ መቁረጥ የሌለብን መሆኑን ነው ። ሲሮጡ መደናቀፍ ፤ መውደቅ መነሣት እንዳለ ማሸነፍና መሸለምም ያለ ነው ።

ታላቁ ሐዋርያ ቅ- ጳውሎስ በ፩ቆሮ- ም- ፱- ቁ- ፳፬ በጻፈው መልእክት « በሽቅድድም ሥፍራ የሚሮጡት ሁሉ እንዲሮጡ ። ነገር ግን አንዱ ብቻ ዋጋውን እንዲቀበል አታውቁምን ? እንዲሁም ታገኙ ዘንድ ሩጡ » ይላል ። « ታገኙ ዘንድ ሩጡ »የሚለው ሐረግ ታላቅ ቃለ አዋዲ ነው ። የሰው ሕይወት የሩጫ ዘመን ነው ። እርግጥ ከልብ ከታሰበበት የሮጠይቀድማል ፤ የታገለም ያሸንፋል ።ዛሬ የውድድሩ መስክ ብዙ ነው ። በትምህርት ፤ በልዩ ሙያ ፤ በሥልጣን ፤በኑሮ ደረጃ ያለው ውድድር ከሩጫ የሚገኝ የሥራ ውጤት ነው ።

እንግዲህ ወንጌላዊው ዮሐንስበጸሎትና በሱባኤ ተጠምዶ የሽምግልና ዘመኑን በደሴተ ፍጥሞ በሚያሳልፍበት ጊዜ « አዲስ ሰማይንና አዲስምድርን አየሁ » ብሎ በራእዩ እንደጻፈው እኛም ሰውነታችንን መርምረን የጐፉየውን ኑሮአችንን አውልቀን ጥለን በዚህ አዲስ ዓመት አዲስ ሕይወት ለመጐናጸፍ እንነሣ ፤ ዓላማችንንም ከግቡ ለማድረስ እንጣር ፤ እንጋር ።

በተረፈ አዲሱ ዓመት ፲፱፻፸፰ዓ.ም. ያጣ የሚያገኝበት ያዘነ የሚጽናናበት፤ የተጣላ የሚታረቅበት ፤ በጠቅላላው የሰላምና የጤና ዘመን እንዲሆንልን እንመኛለን ።



# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያት

ሐዋርያት ማለት « ሂዱና አስተምሩ፤ አጥምቁ » በተባለው ትእዛዝ መሠረት ከአንዱ ዓለም ወደ ሌላው ዓለም ለወንጌል መልእክት የሚሔዱ ከሀገር ወደ ሀገር እየተዘዋወሩ የምሥራችን የሚያበሥሩ የደኅንነትን ትምህርት የሚያስተምሩ ማለት ነው ።

የቃሉ ትርጉም ይህ ከሆነ ዘንድ ለመጀመሪያ ጊዜ ከውጭ ወደ ኢትዮጵያ የተላኩ ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ የሔዱ ኢትዮጵያውያን ሐዋርያት እነማን ነበሩ ?

አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ፣—በመጽሐፈ ምስጢራቸው «ጥምቀትን ያመጣልን የንግሥት ሕንደኬ መጋቢ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ነው» ። በማለት እንደ ጻፉት የመጀመሪያውን ምስጢረ ቤተ ክርስቲያን አምጥቶ በኢትዮጵያ የሰበከ ወይም ያስተዋወቀ ይኸው ጃንደረባው መሆኑ ነው።ጃንደረባው አምኖ መጠመቁና ወደሀገሩ ተመልሶ የተደረገለትን ሁሉ መናገሩ የታወቀ ነው ሰላማም ክርስትናን ለማስተማር ያልተቸገረበት ምክንያት አስቀድሞ በጃንደረባው ተዋውቆ ስለነበር ነው ።

ከውጭ ወደ ኢትዮጵያ ከተላኩት ሐዋርያት መካከል ከጌታችን ደቀ መዛሙርት አንዱ ቅዱስ ማቴዎስ ነው ። ሐዋርያው ማቴዎስ በኢትዮጵያ ወንጌልን አስተምሮና ብዙኃን ሕዝብን አሳምኖ ማጥመቁን የውስጥና የውጭ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሓፊዎች አረጋግጠዋል (ሩፊኖስ ፱-፩) እንድርያስና ቶማስም ወደ ኢትዮጵያ እንደመጡ የተረኩ ሊቃውንት አሉ ።

አንዳንድ ብሔራውያን ሊቃውንትም ቅዱስ በርተሎሜዎስ በሰሜን ኢትዮጵያ ገብቶ እስከ ምዕራቡ ድረስ እያስተማረ ወደ ኑብያ (ሱዳን) መግለቁን ይተርካሉ ። እርሱ ያጠመቀባቸው ወንዞችም የበርት እና ሎሚውሃ እየተባሉ እስከአሁን ድረስ እንደሚጠሩ እነዚሁ ብሔራውያን ሊቃውንት ይናገራሉ ። በዚያ ዘመን ከአፍሪካ ሀገሮች ሁሉ ነፃ መንግሥት ያላት ከውጭ ዓለማት ጋር ግንኙነትን የመሠረተች አምልኮተ እግዚአብሔርን ከክርስትናው ትምህርት በፊት የተቀበለች ሀገር ኢትዮጵያ ስለነበረች ሐዋርያት ወደዚች ሀገር ለመግባት መልካም ዕድል እንደነበራቸው መገመት አያዳግትም ። ስለዚህ ሐዋርያው በርተሎሚዎስ ወደ ኢትዮጵያ እንደገባ በትውፊት የሚነገረው ታሪክ ከእውነት አይወጣም ።

ሌላው ከውጭ የተላከው ሐዋርያ በውጭና በውስጥ ታሪክ የታወቀው ጢሮሳዊው ፍሬምናጦስ ነው ። ጢሮስ በሶርያ ውስጥ የሚገኝ ሀገር ነው ። ቅዱስ ፍሬምናጦስ ወደ ኢትዮጵያ እንዴት እንደመጣ የሚተረከው ታሪክ የታወቀ ስለሆነ በዚህ ጽሑፍ መዘርዘር አያስፈልግም ።

ቅ- ፍሬምናጦስ በ፫፻፴ ዓ-ም- በእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ በቅዱስ አትናቴዎስ ጵጵስና ተሾሞ ወደ ኢትዮጵያ ተላከ በኢትዮጵያ ብርሃነ ወንጌልን ስለአበራ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን ተብሎ በኢትዮጵያውያን ተሰይሞ በአክሱም የመጀመሪያውን ቤተ ክርስቲያን አቋቋመ ምዕመናንን አደራጀ በእምነተ አሪት የነበሩትን ብዙኃን ሕዝብ ወደ እምነተ ወንጌል ለወጠ ፤ ዛሬ ያለውንም ፊደል በሥርዓት አስተካከለ ከምዕመናንም መካከል በወንጌል ማስተማርና በግብረ ክህነት የሚያገለግሉትን መርጦ ሾመ ።

አባ ሰላማ ለመጀመሪያ ጊዜ እየተዘዋወሩ ወንጌልን እንዲያስተምሩና እንዲያጠምቁ ሥልጣነ ክህነት እየሰጠ ሰባት ሰዎችን ሾሞአል ። ሲሾማቸውም ስማቸውን እየለወጠ ሾሞአቸዋል ለምሳሌ ፊንሐስን ተንሥአ ክርስቶስ ፤ አሮንን ሰምዖን ፤ አዛርያስን ፤ ማቴዎስ ፤ አቢሜሌክን ፤ ስብሐት ለአብ ፤ ሄኖክን አማኑኤል ፤ መልከ ጼዴቅን በአሐዱ አምላክ ፤ ሳዶቅን ማዕቀበ እግዚእ በማለት በሐዋርያነት መድቦአቸዋል ።

እነዚህ ሰባቱ ቀሳውስት ከኢትዮጵያ የተነሱ ሐዋርያት ናቸው ፤ ሰባቱ ሐዋርያት እየተዘዋወሩ በሰሜኑክፍል አስተማሩ ብዙ ሕዝብን አሳመኑ ፤ አጠመቁ አብያተ ክርስቲያናትንም አቋቋሙ ።

በሰባቱ ዲያቆናት ምሳሌ (የሐዋ - ፮ ፥ ፩) ሰላማ የሾማቸው ሰባቱ ቀሳውስት ሕዝቡን ማስተማር ብቻ ሳይሆን ቅዱሳት መጻሕፍትን ተርጉመዋል ፤ ሌሎች ለጸሎት የሚያገለግሉ የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍትንም ከውጭ ቋንቋ ወደ ብሔራዊ ቋንቋ ( ግዕዝ ) እየተረጐሙ ጽፈዋል ።

ከዚህ በኋላ እስከ ዘጠኙ ቅዱሳን መምጣት ድረስ ሳዕካነ ጽዮን እየተባሉ ይጠሩ የነበሩ ብዙኃን ኢትዮጵያውያን የወንጌል መምህራን ተነሥተው የክርስትናን እምነት በሰሜን ኢትዮጵያ አስፋፍተዋል ።

ከዚህም ሌላ አባ ሰላማ ፤ በዚያ ዘመን የኢትዮጵያ ግዛት ወደነበረው ወደኖባ ፤ ኢኑኖና መርዌ አምስት ቆሞሳትን ልኮ ትምህርተ ክርስትና እንዲነገር አድርጎ እንደነበር ዶክተር ዛህርያድ የአፍሪካ ጥናት ፕሮፌሰር (ካይሮ) ጽፎአል ።

ዘጠኙ ቅዱሳን ግን ክርስትናውበተሰበከበት አካባቢ ሥርዓተ ምንኩስናን ከማስፋፋትና ያመኑትን ከማጽናናት በቀር ተዘዋውረው ወንጌልን ያስተማሩ አይመስልም ምክንያቱም ሁሉም አስቀድሞ ክርስትናው በተስ



www.ethiopianorthodox.org

በከበት አካባቢ ይኖሩ ነበር እንጂ ወደ ሌላው ክፍለ ሀገር እንደተዘዋወሩ ታሪክ አልተጻፈምና የክርስትና እምነት ከ፬ኛው ምዕት ዓመት ጀምሮ የመንግሥት ሥልጣን በተስፋፋበት ሁሉ ተዘርግቶ ነበር ። ስለዚህም ከመጠራ እስከ ጊሚራ ከአውላሎ እስከ ደንቢዶሎ ከጸአዘጋ እስከ ወለጋ የክርስትና ትምህርት ተሰብኮአል እንደሐዋርያትም ሆነው ትምህርተ ክርስትናውን ያስፋፉ የነበሩ መሪዎችና ሌሎች ባለሥልጣኖች ሁሉ ነበሩ ፤ከዚህም የተነሳ በስድስተኛው ምዕት ዓመት የነበረው ንጉሥ አፄ ካሌብ የክርስትና ትምህርት እንዲስፋፋ ትልቅ ጥረት አድርጐአል ። ከዚያም እስከ ላስታ መንግሥት ፍጻሜ ድረስ መሪዎች ክህነት ከመንግሥት በመያዝ ትምህርተ ክርስትናውን ከእምነቱ ጋር ሲያስፋፉ ኖረዋል ።

ከ፲፪ኛው ምዕት ዓመት ጀምሮ እስከ ፲፫ኛው ድረስ ብዙኃን ብሔራውያን የወንጌል መምህራን ተነስተዋል እነርሱም አባ ኢየሱስ ሞአ ፤ አባ በጸሎተ ሚካኤል አቡነ ተክለ ሃይማኖት አባ ኤዎስጣቴዎስ አባ ያፍቅረነ እግዚእና ዘዮሐንስ ነበሩ እነዚህ ወንጌላውያን በአንድ ቦታ ሳይወሰኑ በሐዋርያነት ከአውራጃ ወደ አውራጃ ተዛውረው አስተማሩ እነ አቡነ ሰላማና ሰባቱ ወንጌላውያን ባልደረሱበት ሁሉ እየሔዱ ወንጌልን አስተማሩ በተለይም ማንንም ሳይፈሩና ሳያፍሩ ይገስጹ እንደነበር በገድላቸው ተጽፎአል ይልቁንም አቡነ ተክለ ሃይማኖትና አቡነ ኤዎስጣቴዎስ ስመ ጥር ሐዋርያት ነበሩ ተክለ ሃይማኖትም «ሐዲስ ሐዋርያ ዘኢትዮጵያ» ተብለዋል ። ለደቡብ ኢትዮጵያ ትምህርተ ክርስትናን አዳርሰዋል ፤ በኋላም አሥራ ሁለት መምህራንን ሾመው በየአውራጃው ልከዋል አቡነ ተክለ ሃይማኖትና ተከታዮቻቸው ሁሉ ቤተ ተክለ ሃይማኖት በመባል እስከአሁን ድረስ ተለይተው ይታወቃሉ ።

በሰሜኑም ክፍል የኤዎስጣቴዎስ ተከታዮች ቤተ ኤዎስጣቴዎስ ይባሉ ነበር እነርሱም እስከ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሐዋርያዊ ተግባራቸውን ፈጽመዋል ።

በዚህ አንጻር ብዙኃን ብሔራውያን ሐዋርያት እንደነበሩ ለመረዳት አያስቸግርም የክርስትና እምነትም በመላ ኢትዮጵያ የተሰበከው ከውጭ በተላኩ ሐዋርያት ብቻ ሳይሆን በብዛት በኢትዮጵያውያን መሆኑ የተረጋገጠ ነው ።

## ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ የተላኩ ኢትዮጵያውያን ሐዋርያትስ ነበሩ ወይ ? ዛሬስ አሉ ወይ ?

በአምስተኛው ምዕት ዓመት በአፄ ገብረ መስቀል ዘመን ኢትዮጵያውያን ሐዋርያት ወደ ሰሜን የመን ተልከው ብዙኃን አሕዛብን አስተምረውና አጥምቀው አብያተ ክርስቲያናትን ሰርተዋል እስከ ፋጢሞች ዘመነ መንግሥት ክርስትና በኢትዮጵያውያን መምህራን በሀገረ የመን ሲነገር ቆይቶአል ቤተ ክርስቲያኑም «ደብረጽዮን» በሚባል የተሰየመ ነበረ የየመን አብያተ ክርስቲያናት በስምንተኛው ክፍለ ዘመን ሲመዘበሩ የተዘረፉ በግዕዝ የተጻፉ የብራና መጻሕፍት ዛሬ በቅብጥ ሙዝየም በካይሮ ይገኛሉ ።

በ፲፩ኛው ምዕት ዓመት በ አፄ ዳዊት ዘመንም ግማደ መስቀሉ በኑብያ በኩል ወደ ኢትዮጵያ ከመጣ በኋላ አፄ ዳዊት ኢትዮጵያውያን ካህናትን ልከው በመድኃኔ ዓለም ስም በኑብያ ቤተ ክርስቲያን ሠርተዋል ። ምንም እንኳ በኑብያ ቀደም ብሎ ክርስትና ቢሰበክም የተላኩት ካህናት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን ሥርዓትና ባህል ለኑብያ ሰዎች አስተምረዋል ያላመኑትንም እያሳመኑ ሰባት አብያተ ክርስቲያናትን እንዳሳነጹ ስለ አፄ ዳዊት የተጻፈው ታሪክ ያስረዳል ይሁን እንጂ ወደየመንም ሆነ ወደ ኑብያ የተላኩት ወንጌላውያን ካህናት ፳፫ በስም ተለይተው አለመታወቃቸው ፪ኛ በተላኩበት ሀገር የሠሩት ሥራ ሁሉ ተመዝግቦ አለመያዙ የአሁኑን ትውልድ ሳያሳዝነው አልቀረም ሆኖም የእያንዳንዱ ሐዋርያ ስምና ሥራ ተዘርዝሮ አለመጻፉ የታሪኩን እውነተኛነት አይለውጠውም ።

እንደገና በ፳ኛው ምዕት ዓመት አጋማሽ ላይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ወደ ዌስት ኢንዲስ (አሜሪካ) ወደ ሱዳንና ወደ ሎንዶን ወንጌላውያንን ልካ በእነዚያ ሀገሮች ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ለዚያው ሀገር ዜጐች ወንጌልን ታስተምራለች በተለይም የዌስት ኢንዲስ ሕዝብ እንደ ኢትዮጵያውያን ጥቁሮች በመሆናቸው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያትን በደስታ ይቀበላሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንን ባህልና እምነት ይከተላሉ ፤



ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ በምዕራብ ክፍለ ዓለም የኢ. ኦ. ተ. ቤ. ክ. ሊቀ ጳጳስ

ስለዚህም ፴ ያህል አብያተ ክርስቲያናት ተሠርተዋል ፤ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ምዕመናንም ተደራጅተዋል ፤ ለእነዚህም ምዕመናን በ፲፱፻፷፬ ዓ-ም አንድ ሊቀ ጳጳስ የተላከላቸው ሲሆን በ፲፱፻፸፩ ዓ-ም- ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ አንድ ሊቀ ጳጳስ ሾመው ልከውላቸዋል ። ጳጳሱም ቀደም ሲል በሐዋርያነት ተልከው ለ፲፯ ዓመታት ሲያስተምሩ የነበሩ ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ ናቸው ፤ በሱዳንም ላሉት ምዕመናን ብፁዕ ዶክተር አቡነ ገሪማ ተልከዋል።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት በ፲፱፻፸፫ ዓ-ም መጨረሻ ላይ በጂቡቲ የኢትዮጵያ ኦ-ተ-ቤ- ክርስቲያን እንድትቋቋም ስለፈቀዱ ወዲያውኑ በጳጳስ ደረጃ አንድ ሐዋርያ በጂቡቲ ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ምእመናን ሾመውላቸዋል ፤ እርሳቸውም ብፁዕ አቡነ ኤልያስ በጂቡቲ የኢት-ኦ-ተ-ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ ናቸው ።



ብፁዕ አቡነ ኤልያስ
በጂቡቲ የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ. ጳጳስ

ብፁዕ አቡነ ኤልያስ ሐዋርያዊ ተግባራቸውን ለመፈጸም ምእመናኑን ከማስተማራቸው ጋር በአሁኑ ጊዜ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያንን በማሠራት ላይ ይገኛሉ ።

በሎንዶንም ባለችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያና ወንጌላዊ ሆነው የሚያገለግሉ አባ አረጋዊ ወልደ ገብርኤል ናቸው ።

## ከውጭም ሆነ ከውስጥ የተላኩት ሐዋርያት ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተውት ቅርስ ምንድን ነው ?

አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ እምነተ ክርስትናን የተቀበለው ከኢትዮጵያውያን ሐዋርያት በመሆኑ ያለምንም ቅሬታ እምነቱን አጽንቶ ምግባሩን ጠብቆ ኖሯል ይኖራልም ።

ከዚህም ጋር ብሔራውያን ሐዋርያት ብሔራዊ ሥርዓትን ባህልን በራስ ቋንቋ ማንኛውንም ትምህርት መጠቀምን ፤ ፊደልንና ቋንቋን ብሔራዊ ዜማንና ወዘይመስሎ ጠብቀው ለተከታዩ ትውልድ አውርሰዋል ።

በውጭ ሚስዮኖች ትምህርተ ክርስትና የተሰበከላቸው ሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች የራሳቸው የሆነውን ሁሉ ለይተው በባዕድ ቋንቋ ይጽፋሉ ያነባሉ ይዘምራሉ ፤ በዚህም ምክንያት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ይቀናሉ በሌላም በኩል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አፍሪካዊት በመሆንዋ ይኩሩባታል ።

የቀደሙት ሐዋርያት እላይ በአጭሩ የተገለጸውን ሠሩ አስተማሩ ዛሬ በጥቅም ላይ ያለውን ታሪካዊ ቅርስሁሉ ጠብቀው አወረሱ እንግዲህ የሚፈለገው የቀደሙትና ዛሬም የአሉት የሐዋርያትን አሠር የሚከተል ነው ።



አባ አረጋዊ ወልደ ገብርኤል በሎንዶን የኢ. ኦ.ተ.ቤ.ክ. ሐዋርያ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት እስካሁን የተጠቀሰውን አሰረ ሐዋርያት በመከተል ከ፲፱፻፶፯ ዓ- ም- ጀምሮ በተለያየ መንገድ ወንጌልን ያስተምራል በየክፍላተ ሀገሩ በተዘዋዋሪ ቡድን ሲያስተምር በአንዳንድ ቦታዎች ደግሞ ቀዋምያን



ብፁዕ አቡነ በርናባስ በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት ሊቀ ጳጳስ

የወንጌል መምህራንን መድቦ የወንጌልን ትምህርት በማስፋፋት ላይ ይገኛል ለምሳሌ በጐጃም በመተከል አውራጃና በከፋ በጪብራ ወረዳ ነዋሪነታቸው በዚያው የሆነ ወንጌላውያንን አሰማርቶአል ። በእነዚህም ቦታዎች ከሚኖሩ ሻንቅላና ቲሻና ብሔረሰቦች መካከል ወደ ክርስትና እምነት የተመለሱትን አንዳንድ ወጣቶች ወደ አዲስ አበባ በማምጣት ዘመናዊውንና መንፈሳዊውን ትምህርት በማስተማር እስከ ዩኒበርስቲ ደረጃ አድርሶአል ።

የድርጅቱ ሐዋርያዊነት በገጠርና በከተማ በቤተሰብም ስለሆነ በገጠረ ኢትዮጵያ ለሚኖሩ ወገኖች መምህራንን ልኮ ሲያስተምር በውስጡ ያሉት



www.ethiopianorthodox.org

ሠራተኞችን ደግሞ ገንዘብ እየከፈለ እስከ ዩኒቨርስቲ ደረጃ አብቅቶአል ካልተማሩ አያስተምሩምና ።

ሐዋርያዊ ድርጅት በዚህ ተግባሩ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የማን ብርሃን ዓይን ሆኖ ለ፳ ዓመታት ቤተ ክርስቲያንዋ ልትሰለፍበት በሚገባው ሜዳ ሁሉ በመሰለፍ ሲሠራ በመልካም አርአያነቱም ሲያበራ ቆይቶአል ። ዛሬምየጥንቱን ግብረ ሐዋርያት እየተረጐመ የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሕልውናን በአደባባይ ይመሰክራል ። ምስክርነቱም የታመነ ነው።

ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ ።

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ . . .

ከ፩ኛው ገጽ የዞረ

ስያን በመላክ በሥነ ጽሑፍ በነገረ መለኮት በምሥጢረ መለኮት ፤ በስብከት ዘዴ በማሠልጠን ላይ ይገኛል።

## የማከፋፈያ ኮሚቴ

ይህ ኮሚቴ ድርጅቱ የሚያሳትማቸውን ልዩ ልዩ ጋዜጦችና መጽሔቶች ፤ ልዩ ልዩ ጽሑፎች በወቅቱ ለአ



ቆስ መክብብ አጥናው የድርጅቱ ረዳት ተጠባባቂ ሥራ አሥኪያጅ ፤

ንባብያን እንዲደርሱ ያደርጋል ፤በቅርስነት የሚቀመጡት ጋዜጦችና መጽሔቶች ተጠርዘውና በክብር ተጠብቀው እንዲቀመጡ ያደርጋል ። የመጽሔትና ጋዜጣ ደንበኞች ዓላማውን ተረድተው እንዲመዘገቡ ያደርጋል ። የተመዘገቡት ማኅበርተኞችም በወቅቱ እንዲደርሳቸው ሲያደርግ በአጠቃላይ የድርጅቱ ሥነ ጽሑፍ ኮሚቴ የሚያሳትማቸው ጽሑፎች በአንባቢዎች እጅ እንዲገቡ ማንኛውንም ጥረት የሚያደርግ ክፍል ነው ።

## የፎቶ ግራፍ እስቱዲዮ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት የራሱ የሆነ የፎቶ ግራፍ እስቱዲዮ አለው ።

በዚህም መሠረት ፎቶግራፎችን ያነሣል ። በራሱ እስቱዲዮ ፎቶ ግራፎችን ያትማል ። ጥንታውያን የቤተ ክርስቲያን ቅርሶችን ፤ ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናትን ፎቶግራፍ ያነሣል ፤ ለጋዜጣና መጽሔት የሚሆኑትን በጋዜጣና በመጽሔት ያወጣል። ለቅርስነትም በእስቱዲዮው በቅርስነት ያስቀምጣል ።



አቶ መኩሪያ አበጋዝ የድርጅቱ ዋና ጸሐፊ

እስላይድ ፊልሞችንም በማንሳት በፊልም ለምዕመናንያሳያል የጥንታዊት ቤተ ክርስቲያንንም ቅርሳቅርስና ንዋያተ ቅድሳት በቅርስነት በእስላይድ ፊልም አያነሣ በእስቱዲዮ ያስቀምጣል ። በየታላላቅ በዓላትም ለምዕመናን ያሳያል ።

ወደፊትም ተንቀሳቃሽ የፊልም ፕሮጀክት በማስመጣት ይህንኑተግባሩን ለማስፋፋት ከፍተኛ ዕቅድአለው።

## ክፍል ፫ ፤
## ትምህርት ቤቶች

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች አንዱ ፤ ትምህርትን ማስተማር እንደመሆኑ፤ መጠን በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ ሳይገታ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ትምህርት ቤቶችን በማቋቋም ጭምር ነው ።በዚህም መሠረት የድርጅቱ የትምህርት ክፍል ዘመናዊውንና ጥንታዊውን ትምህርት አጣምረው የሚያስተምሩ ትምህርት ቤቶች የሚቋቋሙበትንና የሚስፋፉበትን መንገድና ዘዴ በማጥናት እስከአሁን ከዚህ የሚከተሉትን ት/ ቤቶች አቋቁሞ ለአዲስ አበባና ት/ ቤት በሌለባቸው በአንዳንድ ክፍሎች የገጠሪቱ ኢትዮጵያ ከፍተኛ አገልግሎት ሲፈጽም ቆይቷል ።

## ፩—አዲስ አበባ

በ፲፱፻፵፯ ዓ· ም· ለመጀመሪያ ጊዜ በመንበረ ፀባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ጽ/ ቤት ግቢ ውስጥ ት/ ቤት ከፍቶ ፭ ያህል መነኮሳት ቀሳውስት፤ ዲያቆናትና መዘምራን ካላቸው መንፈሳዊ ትምህርት ጋር የ፩ኛ ደረጃን ትምህርት በዘመናዊ ሁኔታ እንዲማሩ ሐዋርያዊ ድርጅት ከፍተኛ ጥረት አድርጎ የድርጅቱ የድርሰትና ሥነ ጽሑፍ ሠራተኞችም በትርፍ ጊዜያቸው በማስተማር ምንም ዓይነት ዋጋ የማይከፈልበት ነፃ ትምህርት ቤት እንዲሆን ጥረት አደረጉ ። ከዚያም የተማሪዎች ቁጥር እየበረከተ ስለሔደ ድርጅቱ ከ፱ ሽህ ብር በላይ ወጭ አድርጎ በዘመናዊ ፕላን አሁን «ሥላሴ ት/ ቤት» ያለበትን ሕንፃ አሠርቶ ዘመናዊውን ትምህርት ከጥንታዊው የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ጋር በማዋሐድ እያስተማረ እስከ ፰ኛ ክፍል ከፍቶ መምህራንን ቀጥሮ በማስተማር ከፍ ያለ አስተዋጽኦ አበርክቷል ። ብዙ ኢትዮጵያውያንም በዕውቀት እንዲበለጽጉ ያልተቆጠበ ጥረት አድርጓል ።

ድርጅቱ በዚህ ብቻ ሳይገታ ከተፈቀደለት የመተዳደሪያ በጀቱ ላይ በየጊዜው እየቆረጠ የመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ያስቀረበት ብር ፷፭ሽህ (ስድሳ አምስት ሽህ ብር) ተሰጥቶት ሌላ የልጃገረዶች ት/ ቤት ለማቋቋም በዝግጅት ላይ ሳለ ፤ ካቴድራሉ ት/ ቤቱን ከድርጅቱ ወስዶ ወደራሱ ንብረትነት ስላዛወረው እቅዱ ሁሉ ሳይሳካ ቀርቷል፤ ያም ሆኖ ድርጅቱ ት/ ቤቱን በሚያካሒድበት ወቅት ያሳየው የሥራ ውጤት በቀላል የሚገመት አይደለም

ሐዋርያዊ ድርጅት በዚህ ት/ቤት

## ያሳየው የሥራ ውጤት

፩· ቀደም ሲል በሀገር ትምህርት የበሰሉትን ምሁራን በማሰባሰብ ድርጅቱ ወደዚህ ት/ ቤት እያስገባ በዘመናዊ ትምህርትና በመንፈሳዊኮርስ እያሠለጠነ በሥራ የመደባቸው መምህራንና ደራሲያን አሁንም በተመደቡበት የሥራ መስክ እያገለገሉ ይገኛሉ ።

፪· ድርጅቱ በዚሁ ት/ ቤት ካስተማራቸው መነኮሳትና ዲያቆናትመካከል ብዙዎቹ ወደውጭ ሀገር ተልከው ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ሲሆኑ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁትም ወደ ሀገራቸው ተመልሰው በከፍተኛ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ላይ ናቸው ። ከእነሱም መካከል ጳጳሳትና ሊቃነ ጳጳሳት ይገኛሉ ።

፫· በሀገር ውስጥም ቢሆን የ፪ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀው በሥራ የተሠማሩት ፤ ወደዩኒቨርሲቲ በመግባት ዲግሪያቸውን ተቀብለው በከፍተኛ ኃላፊነት ላይ የሚገኙ ዲያቆናትም በርካታ ናቸው ።

## ፪· ወልመራ ጉንቱታ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ትምህርት ቤት ባልተቋቋመባቸው ቦታዎች ለማቋቋም ባለው ዕቅድ መሠረት በሸዋ ክፍለ ሀገር በመናገሻ አውራጃ በወልመራ ወረዳ በጉንቱታ ቀበሌ እማሆይ ደብሪቱ ጠብቃቸው በሰጡት ፩ሽህ ካሬ ሜትር ቦታ ላይ



የወልመራ ጉንቱታ ት/ቤት መምህራን

በ፲፱፻፶፯ ዓ· ም· የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አቋቁሞ ለ፲፯ ዓመታት ያህል በአካባቢው ለሚገኙት ወጣቶችና ጐልማሶች ዘመናዊና ጥንታዊ ትምህርት ሲያስተምር ቆይቷል ።

እማሆይ ደብሪቱ ለትምህርትቤቱ ከሰጡት ፩ሺህ ሜትር ካሬ ቦታ ጋር አምስት ክፍል ቤቶችን ጨምረው የሰጡ በመሆናቸው ድርጅቱ በነዚሁ ክፍሎች ሲያስተምር ከቆየ በኋላ ት/ ቤቱ እያደገ ሲሔድ ሌሎች ተጨማሪ ክፍሎችን ሠርቶ ጥንታዊና ዘመናዊ ትምህርትን የማስተማር ችሎታ ያላቸውን መምህራን በተጨማሪ እየቀጠረ የማስተማር ሥራውን በተቀላጠፈ ሁኔታ ሲያከናውን ቆይቷል ። በዚህም መሠረት የ፩ኛ ደረጃ ተማሪዎችን ብሔራዊ ፈተና ማስፈተን ከጀመረበት ከ፲፱፻፷፰ ዓ· ም· ጀምሮ እስካሁን ድረስ ተማሪዎቹ ከፍተኛውጤት ስለሚያመጡ በአውራጃው ውስጥ ካሉት ት/ ቤቶች በደረጃው ከፍተኛ ውጤትን ሲያስገኝ ቆይቷል ። ቀጥሎም በ፲፱፻፸፫ ዓ· ም· የመለስተኛ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት በዚሁ ት/ ቤት በተጨማሪ እንዲከፈት አድርጎ በመካሔድ ላይ ሲሆን ፤ በዚህም ቢሆን ውጤቱ የሠመረ ሆኗል ።

ለምሳሌ በ፰ኛ ክፍል በ፲፱፻፸፭ ዓ· ም· ከመጀመሪያዎቹ ተፈታኞች



www.ethiopianorthodox.org

መካከል በመቶ ዘጠና ማለፋቸው ዓይነተኛ ምሳሌ ሊሆን ይችላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት በሚያካሒደው በዚሁ በአባ ወልደ ማርያምና በእማሆይ ደብሪቱ ጠብቃቸው ስም በተሰየመው ት/ቤት በአሁኑ ጊዜ ፲ መምህራንና አንድ የጥበቃ ሠራተኛ የሚገኙ ሲሆኑ ፤ ስድስቱን መምህራን በበጀት ቀጥር የሚያ



አቶ ሐዲስ ተረፈ በወልመራ ት. ቤት የ፲፱፻፸፬ ዓ. ም. ትምህርታቸውን በከፍተኛ ውጤት ለአጠናቀቁ ተማሪዎች ሽልማት ሲሰጡ ።

ሠሪቸው ድርጅቱ ነው ። አራቱደግሞ ኤትምህርት ሚኒስቴር ተልከው በዚሁ ት/ ቤት እንዲያስተምሩ የተመደቡ ናቸው ። በ፲፱፻፸፬ ዓ· ም· የትምህርት ዘመን ከ፫፻ በላይ የሚሆኑ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ተከታትለዋል።

## ፫· ወላይታ ሶዶ

የወላይታ አውራጃ ሐዋርያ የነበሩት አሁን ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ካሠሯቸው ፳፬ ት/ ቤቶች አንደኛው በሆነው በዚሁ በወላይታ አውራጃ በሶዶ ከተማ አካባቢ ቆንቶ በተባለው ቦታ ቅዱስነታቸው በዚያን ጊዜ በመሠረቱት ትምህርት ቤት መምህራንን በመላክና፲፬ሽህብር የበከሉን ወጭ አድርጎ ት/ ቤት በማሠራት ከ፲፱፻፶፰—፲፱፻፶፱ ዓ/ ም· በመተባበር ሲሠራ ከቆየ በኋላ ት/ ቤቱ በዚያ ጊዜ ቅዱስነታቸው ይመሯቸው ከነበሩት ሌሎች ት/ ቤቶች ጋር እንዲመራ ስለተደረገ ድርጅቱ በሌሎች ክፍላተ ሀገር ሌሎች ት/ቤቶችን የማቋቋም ሥራውን ቀጥሏል ።

## ፬· መተከል ቡለን

በጎጃም ክፍለ ሀገር በመተከል አውራጃ በወንበራ ወረዳ ቡለን አካባቢ ቀደም ሲል ትምህርት ቤት ባለመኖሩ በዚያ የሚኖሩት የሺናሻ የኦሮሞና የሻንቅላ ብሔረ ሰቦች እንኳንስ የትምህርትን ጥቅም ወሬውንም ስምተው የማያውቁ ስለነበሩ በተለይ የሻንቅላ ብሔረ ሰቦች ከሥልጣኔ ዓለም ተገልለው ልብስ የመልበስ ዕውቀት እንኳ ተሰውሮባቸው ይኖሩ እንደነበር የታወቀ ነው ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት ይህንን ችግርበማጥናት በ፲፱፻፶፰ ዓ· ም· በመተከል ቡለን የ፩ኛ ደረጃ ት/ ቤት እንዲቋቋም· አድርጎ የማስተማር ሥራውን ለጊዜው በሦስት መምህራን ማካሔድ ጀመረ ።

የትምህርት ቤቱ ደረጃ እያደገና የተማሪዎቹም ቁጥር እየጨመረሲሄድ በየዓመቱ ተጨማሪ መምህራንን በመደብ ሥራውን አስፋፍቶ በ፲፱፻፸፭ ዓ· ም· የመጀመሪያዎቹን ተፈታኞች ለብሔራዊ ፈተና አስቀምጦ በአጥጋቢ ውጤት እንዲያልፉ አድርጓል ። ስለዚህም በአካባቢው ኗሪዎች ዘንድ የትምህርት ጥቅም እየታወቀ በመሔዱ በዚያን ጊዜ በዚህ ት/ ቤት ይማሩ ከነበሩት መካከል ብዙዎች ወደ ዩኒቨርሲቲ ገብተው ከፍተኛ ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ይገኛሉ ። በልዩ ልዩ የሥራ መስክ የተሠማሩትም ብዙዎች ናቸው ። በተለይ ከሻንቅላ ብሔረ ሰቦች መካከል አንዳንዶቹን ድርጅቱ ወደአዲስ አበባ አስመጥቶ እየረዳ በማስተማር ላይ ይገኛል ።

## ድርጅቱ ለአካባቢው ኅብረተሰብ የሰጠው ጥቅም

ሀ—በዚያ ወረዳ ያሉት ብሔረሰቦች ኋላ ቀር በሆነ ባህልና በድንቁርና ሰንሰለት የታሠሩ በመሆናቸው ድርጅቱ በዚያ አካባቢ ት/ቤት በማቋቋሙ የሥልጣኔን ጭላንጭል እንዲያዩና የማኅበራዊ ኑሮንም ጥቅም እንዲረዱ በማድረግ የት/ ቤቱ መምህራን ከፍ ያለ አስተዋጽኦ አድርገዋል ።

ለ—ልብስ መልበስን ለማያውቁት ድርጅቱ በነፃ እያለበሰ የልብስን ጥቅም እንዲረዱ አድርጓል ። ለምሳሌም ያህል በ፲፱፻፶፱ ዓ· ም· ከቀይ መስቀል ጋር በመጻጻፍና በመተባበር ለ፭፻ የሻንቅላ ብሔረ ሰቦች የተለያዩ ልብሶችን በነፃ ሰጥቷል ።

ሐ— እርሻን የማያውቁት አርሰው መጠቀምን እንዲለምዱ ለማድረግ ድርጅቱ የእርሻ መሣሪያዎችንና በሬዎችን ገዝቶ በመስጠት መምህራኑ በትምህርት ቤቱ አካባቢ የሠርቶ ማሳያ ቦታ አዘጋጅተው እያረሱ መልካም አርአያ እዲንሆኑ በማድረጉ የተለያዩ የእህል ዓይነቶችን በመዝራትና በማምረት ፓፓዩና ሙዝ የመሳሰሉ

ተከታዩ ወደ ገጽ ፴ ዞሯል



# የሰንበት ትምህርት ቤት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

ከአቶ አእምሮ ማንደፍር
(ከድርጅቱ መሥራች ሠራተኞች አንዱ)



የሰንበት ት/ ቤት አመሠራረትና ይዘት ከሃይማኖት ድርጅቶች አንድዋ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ሕልውናዋን ካሳወቀችና ካስተማመነች በኋላ ዶግማዋን ለማስፋፋት ጥናታዊ ዕቅድ አውጥታ ተግባራዊ ማድረግ ስትጀምር ከተጠቀመችባቸው የማስተማሪያ ዝግጅት ዘይቤዎች አንዱ ሆኖ የተጸነሰ ነው ማለት ይቻላል ።

ጥንስሱ በዚህ ዓይነት ቀደም ብለው ከሚታወቁት የቤተ ክርስቲያን ትምህርት መስጫ ተቋሞች አንዱ ሆኖ ቢገመትም ከሂደቱና ከውጤቱ አኳያ ሲገመገም ደግሞ የሳይንሣዊ ፍልስፍና እየተስፋፋ መጥቶ ሕብረተሰቡን ማጥለቅለቅ ሲጀምር ቀደም ሲል በአብዛኛው የቀለም በመጠኑም የተግባረዕድ ትምህርት ኃላፊ በመሆን የክርስቲያኑን ኅብረተሰብ ትመራ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖታዊ ግንዛቤ ከሕዝቡ አዕምሮ እንዳይለይ የሰንበት ት/ ቤትን ማቋቋም ጠቃሚ ሁኖ አግኝታዋለች ።

በመሠረቱ በአጋጣሚም ይሁን በራሷ በቤተ ክርስቲያን ጥረት በክርስቲያኑ ዓለም የዕለተ እሑድ ሕዝባዊ በዓል መሆን ለርሷ ትልቅ ጥቅም ሰጥቷል።ምክንያቱም ከአምስት ወይም ከስድስት የሥራ ቀናት በኋላ ሠራተኛው ዕረፍት የሚያገኝበት ዕለት እንደመሆኑ በጉልበት ሥራና በሳይንሳዊ ምርምር ተሠማርቶ በትጋት ሲሠራ የሰነበተው ሠራተኛ በሰባተኛው የዕረፍት ቀን ከዚያ ከተለመደውና ሥጋዊና ጊዜያዊ አስተሳሰብ ወደ ረቀቀና ዘለዓለማዊ ተስፋ ወደሚሰጥ መፈላሰፍ መሸጋገር የሚያደክምና የሚያሰለች ሳይሆን መንፈስን የሚያድስ ሆኖ ስለሚያገኘው በጉጉት ይከታተለዋል በሃይማኖት ፍልስፍና የበሰሉ ምሑራን ከተገኙማ « ሚዳውም ይኸው ፈረሱም ይኸው » እንደሚባለው ነው ።

በአጠቃላይም የሰንበት ት/ ቤት የማስተማር ዘይቤ በሚገባ ከተግባር ላይ ከዋለ ከሕፃንነት እስከ ሽምግልና ባለ የዕድሜ ደረጃ ሁሉ ሊሠራበት የሚችል ነው ። በትምህርት ደረጃ በኩልም የሃይማኖት ትምህርት ብቻ ሳይሆን መጀመሪያ በሳይንስ በቁጥርና በአጠቃላይ ፍልስፍና ገፍተው በሁለተኛ ደረጃ በሃይማኖት ፍልስፍና የበሰሉ በሁለቱም ስፋትና ጥልቀት ያላቸው ረቂቁን ከግዙፉ አዛምደው በማቅረብ በሥነ ልቡና ዘይቤ ማስረዳትና ማርካት የሚችሉ የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ከተገኙ ከሥጋዊ ትምህርት ጋር የሃይማኖት ትምህርትም የሚሰጥበት ዘዴ ነው ። የሰንበት ት/ ቤት በዚህ ዓይነት ከፍ ያለ ተግባር የሚከናወንበት እንጂ ምንነቱን ያልተረዱ እንደሚገምቱት መዋዕለ ሕፃናት አይደለም ።

ስለዚህ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ተሰጠውን (ቅዳሴውን) ዜማውን ማንኛውንም የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ወደ አማርኛ እየተረጎሙ ለጥናት ከትትል አመቺ አድርጎ በማቅረብ ምዕመኑን በጾታ ሳይለዩ ወደ ቤተ ክርስቲያን በመጋበዝና በማሰባሰብ ማስጠናት፡ማስተዋወቅ፡በርን መክፈትና ግቡ ማለት በጣም አስፈላጊ ነው ።

አስፈላጊነቱን ብዙዎች ተገንዝበውት ነበር ቢባልም ያጀማመሩ ሁኔታ በሥራ ሊተረጐም የቻለው ግን በ፲፱፻፶፩ ዓ· ም በተቋቋመው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅትና በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል አስተዳደር ከፍተኛ ጥረት ነበር ።

ምንም እንኳን ከያዝነው መቶ ዓመት አካባቢ ጀምሮ በቅዳሴ ውዳሴ መካከል አንዳንድ ጣልቃ ገብ የአማርኛ ምንባብ ማሰማት ብትጀምርም ጠቅላላ አገልግሎቷን በግዕዝ ቋንቋ ስታካሂድ ዘመናትን ባሳለፈችው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክር



www.ethiopianorthodox.org

ስቲያን ውስጥ ተጠቃሹ ድርጅት አንዳንድ የጊዜውን ሁኔታ መገንዘብ ከሚችሉ አዛውንት ምእመናን ጋር ስለ አስፈላጊነቱ በመወያየትና የበጎ ተግባር አንድነት በመፍጠር መጀመሪያም የነርሱን ልጆች ለምሳሌነት በግንባር ቀደም በመሰብሰብና ከላይ የተዘረዘረውን ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ውዳሴ በአማርኛ ማስጠናትና በታላቁ ካቴድራል በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ማዘመር ሲጀምር ያ ከግዕዝ በስተቀር በሌላ ቋንቋ የተደረገ ጸሎት ቅድመ እግዚአብሔር መድረሩን ያልተረዳ ያ ልዩ ልዩ የአማርኛ መዝሙርና ምንባብ የቤተ ክርስቲያን የዱሮ የቆሎ ተማሪዎች ባልሆኑ ወጣቶች ይባስ ተብሎ በተለይ በሴቶች ልጆች ሲዘመር ሰምቶ የማያውቅ የአንዳንድ ምዕመናን ጆሮ በጣም እንግዳ ሆነበት ለመቀበልም ተቸገረ አንዳንዶቹ ምኑን አሰማኸኝ ? እያሉ ቅድስት ሥላሴን ትተው ይህ የሴቶች ልጆች የዝማሬ ድምፅ ወደማይሰማበት ቤተ ክርስቲያን ከመሰደዳቸውም በላይ ሴቶች ቀደሱ እያሉ በማስወራትም የኦርቶዶክስ ን ምእመናን ግራ ማጋባት ተጀምሮ ነበር ። ከካህናቱም በተለይ ከመዘምራኑ አንዳንዶቹ የግዕዙን መዝሙር ወደ አማርኛ ተመልሶ በተለይ በሴቶች ልጆች ሲዘመር በመስማታቸው ቃለ እግዚአብሔር እንደረከሰ እነርሱም እንደተጠቁ አድርገው መመልከታቸው ልጆቹንና ቋንቋውንም በአንድነት እንደጠሉት መቋጠራቸው አልቀረም ።

ሆኖም ለውጥ በመሠረቱ ጥሩውን ከመጥፎው ለይተው ማየት በማይችሉ የአጉል ባህል ተገዥዎች ዘንድ ተቀባይነት ማጣቱ እንደማይቀር የትናንቱም የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ጠቃሚውን ሳይንሳዊ ጥበብ የሚያጐናጽፈውን ዘመናዊ ትምህርት እንኳን ለመቀበል ምን ያህል ያገረግር እንደነበር ስለአልተረሳ በአዋቂዎች ዘንድ አስገራሚ ሆኖ አልተገኘም ። ለማለማመዱ ጥረት ማስፈለጉ ታምኖበት ይሰነዘር በነበረው ነቀፌታ ወደኋላ ሳይባል ወደፊት ስለተገፋበት ብዙ ወጣቶችን በማሰልጠን የካቴድራሉ ምዕመናን እንዲለማመዱት ሌሎች አድባራትም እንዲከተሉት ለማድረግ ተቻለ ።

ከላይ የተጠቀሱትንም የትምህርት ዓይነቶች ወጣቶቹ እንዲከታተሏቸው በአማርኛ አዘጋጅቶ ማቅረቡ ቀላል አልነበረም ። ግን አስፈላጊነቱን በማመን በራሳቸው ንቃተ ሕሊና ተገፍተው የሚሠሩና ችሎታም ያላቸው ዘመናውያን ወጣቶች በድርጅቱና በአጠቃላይም በካቴድራሉ ይገኙ ስለነበር ዕቅዱ በተግባር ሊተረጐም በቅቷል ።

በውጤቱም በኩል ስንመለከት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ት/ ቤት በመሠረተ ዓላማውና በዓለም አቀፍ ይዘቱ አኳያ ሲታይ ዕድገቱ መጠነኛ ቢሆንም ድርጅቱ በሃያ ዓመት ዕድሜው የሰንበት ት/ ቤትን በማቋቋም ረገድ የሰጠው አገልግሎት በቀላሉ የሚገመት አይደለም ። ምክንያቱም ይህ ድርጅት የዛሬ ሃያ ዓመት በቅድስት ሥላሴ የመሠረተውን ዓላማና አርአያ በመከተል ዛሬ አሥራ አራቱም አህጉረ ስብከቶች በየቤተ ክርስቲያኑ የሰንበት ት/ ቤት አቋቁመው ይገኛሉና ነው ።

## የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ . . .

ከገጽ ፳፰ የዞረ

ትን አትክልት በመትከል ጠቃሚ ትምህርት በመስጠታቸው በአሁኑ ጊዜ ሕዝቡ እያረሰና እያመረተ መጠቀምን ለምዶ የእርሻን ሥራ ራሱ እያካሔደ ጥሩ ውጤትን አሳይቷል ።

መ—የድርጅቱ መምህራን በዕረፍት ጊዜያቸው እሑድና ቅዳሜ እየተዘዋወሩ ወንጌልን በመስበክ በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎችን ወደ ክርስትና እንዲመለሱ አድርገዋል ።

### ፳- አዋሽ ደብረ ፀሐይ

በሸዋ ክፍለ ሀገር በመናገሻ አውራጃ በዓለምገና ወረዳ ወላይታ ሶዶ መንገድ በአዋሽ መልካ ቁንጡሬ ወንዝ አጠገብ ባለችው የደብረ ፀሐይ ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢውስጥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት በ፲፱፻፷፬ ዓ- ም- የ፭ኛ ደረጃ ት/ ቤት አቋቁሞ በማስተማር ኅብረ ተሰቡን ሲያገለግል ቆይቷል ። ሆኖም የተማሪዎች ብዛት እየጨመረ ሔዶ የትምህርት ቤቱ ዕድገት በመቀጠል ላይ ሳለ ትምህርት ሚኒስቴር ከአጠገቡ ሌላ ት/ቤት ስለከፈተ ከ፭ኛ እስከ ፮ኛ ክፍል ያሉትን ተማሪዎች ለትምህርት ሚኒስቴር አስረክቦ መምህራኑን ወደ ሌላ ቦታ መድቧቸዋል።

የትምህርት ቤቱ መምህራን ለአካባቢው ሕዝብ የሰጡት ጥቅም

ሀ—የድርጅቱ መምህራን ከመደበኛ ሥራቸው መልስ ከቀኑ ፲ ሰዓት እስከ ምሽቱ ፫ ሰዓት ድረስ በየቀኑ የአምስት ሰዓት ነፃ ትምህርት በመስጠት ማይምናን በመሠረተ ትምህርት እየሠለጠኑ ማንበብና መጻፍ እንዲሁም የሒሳብ ስሌት ትምህርት እንዲያጠኑ በማድረግ የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ ከመጀመሩ ከሰባት ዓመታት በፊት ለኅብረተሰቡ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል ።

ለ—ስብከተ ወንጌልን ለማስፋፋት በትርፍ ጊዜያቸው በበዓላት ቀን በዚያ አካባቢ ባሉት አብያተ ክርስቲያናት እየተዘዋወሩ አስተምረዋል ።

ሐ—የሰንበት ት/ ቤት በማቋቋም ወጣቶችን በመንፈሳዊ ትምህርት ሲያሠለጥኑ ቆይተዋል ።



# ወላድ ሴት

«አዳምም ለሚስቱ (ሔዋን) ብሎ ስም አወጣ የሕያዋን ሁሉ እናት ናትና » ዘፍጥ- ም-፫- ቁ- ፳

በዚህ ቃል መሠረት አሁን እስካለንበት ዘመን ድረስ ሴቶች ልዩ በሆነ ከእግዚአብሔር በተሰጣቸው ጸጋ ሰውን ያህል ፍጥረት በማኅጸናቸው ተሸክመው በእርሱ ጥበብ ይወልዳሉ ። በእናትነታቸውም ተንከባክበው ያሳድጋሉ ። ይህ ሲባል ከእርግዝና ጊዜ ጀምሮ እስከመውለድና ከዚያም በኋላ ባለው ጊዜ ውስጥ ብዙ ችግር ሊኖር እንደሚችል መገንዘብ ይኖርብናል ። የእናትዬዋንም ሆነ የልጇን ደኅንነትና ጤንነት ለመጠበቅ ደግሞ ሊደረግ የሚገባውን እንክብካቤና ጥንቃቄ መረዳት ተገቢ ነው ።

በመጀመሪያ የእርግዝና ጊዜም ሆነ በአንዳንዶች ላይ እስከሚወልዱ ድረስ አልፎ አልፎ የመበሳጨትና የጠባይ ለውጥ ይታይባቸዋል ። በዚህ ጊዜ ነገሩን በመረዳት በትዕግሥት ለማለፍ እንዲሁም በተቻለ መጠን ለማስደሰት መሞከር ጠቃሚ ነው ። በተለይ ከአንድ እስከ ሦስት ወር ድረስ የማቅለሽለሽና የማስታወክ ሁኔታ ሊኖር ይችላል ። አምሳ በመቶ በሚሆኑ ሴቶች ላይ እንደሚፈጸም ታውቋል ። ይህ ሊሆን የሚችለው በሰውነት ውስጥ በሚፈጠሩ አንዳንድ ለውጦችና በተለይ ሴትዬዋ በቶሎ የምትናደድ ማንኛውም ነገር በቀላሉ ቶሎ የሚሰማት እንዲሁም ከአልጋዋ ላይ በድንገት የምትነሳ ከሆነ ነው ። ትውከቱም ለሰውነቷ ድርቀትን ስለሚያስከትል በምግብ በኩል ጥንቃቄ ወስዶ መከላከል ጥሩ ነው ። ይኸውም ደረቅ ያለ ምግብ በጥቂት በጥቂቱ ቶሎ ቶሎ መመገብ ፤ ከመተኛትዋ በፊት ትኩስ ነገር መጠጣት ወይም ጣፋጭ ነገር መብላትና በተቻለ መጠን ውሃ በብዛት መጠጣት አለባት ። ቅመም የበዛበት ምግብ ግን ባትመገብ መልካም ነው ።

በእርግዝና ወራት የሆድ ድርቀት ፣ የጀርባ ሕመም ፤ የምግብ ፍላጐት መቀነስ ፤ የማዞር ስሜትና እንቅልፍ ማጣት ሊኖር ይችላል ። በምግብ ፍላጐት መቀነስ ሳቢያ የደም ማነስ በሽታ ሊመጣ ይችላል በተጨማሪም ጽንሱ ዕድገቱን የሚያካሂደው ከእናትዬዋ ማንኛውንም ነገር በእንግዴ ልጁና በእትብቱ አማካኝነት እየተላለፈለት በመሆኑ ይህ ሁሉ ሁኔታ እናትዬዋንም ሆነ ልጁን ስለሚጐዳ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው ። ለብዙ ሰዎች ይህ ሁሉ ስለማይታያቸው እርግዝናን እንደቀላል በመቁጠር ደንታ የማይሰጣቸው አሉ ። አንዳንዶቹ ደግሞ በተሳሳተ ልማድ ወተትና ጐመን መብላት ጥሩ አይደለም ብለው ስለሚያስቡ እነኝህን ጠቃሚ ምግቦች የማይወስዱ አሉ። ነገር ግን እነኝህ ምግቦች ለእናትዬዋ የሆድ ድርቀትን ለመከላከልና ለበሽታም ኃይል እንዲኖራት ለማድረግ ሲረዱ ለልጁ በተለይ ወተት ለአጥንቱና ከተወለደ በኋላ ጥርስ በጊዜው እንዲያወጣ ይረዳዋል ።

አንዳንድ ሥራዎችን መሥራት የግድ ቢሆንም በጣም አድካሚ የሆነ ሥራ በአንድ ቀን መሥራት ጉዳት ሊያስከትል ስለሚችል መከፋፈልና በፕሮግራም መሥራትና በቂ ዕረፍት ማድረግ ጠቃሚ ነው ። የልጁ ዕድገትም እየጨመረ ሲሄድ ድካሙ ሊጫጫን ይችላል ። ወደ መጨረሻው የእርግዝና ወራትም አልፎ አልፎ ለመተንፈስ የሚያስቸግርበት ጊዜ አለ ይህም የሚሆነው ጽንሱ ወደላይ በመግፋቱ ሲሆን ከጥቂት ጊዜ በኋላ ወደ ታች ስለሚወርድ ችግሩ ይወገዳል ። በተቻለ መጠን የሰውነትንና የልብስን ንጽሕና መጠበቅ በጣም ተገቢ ነው ሆድ እንዲያጠራ ተብሎ ወይም የኮሶ ትል ይዞኛል በማለት ያለሐኪም ትዕዛዝ የሚወሰድ መድኃኒት ከፍተኛ ጉዳት ሊያመጣ ስለሚችል እናቶች ከዚህ ድርጊት ቢቆጠቡ መልካም ነው ።

በዚህ የእርግዝና ወራት ሊፈጠሩ የሚችሉ ሌሎች ችግሮችም አሉ ። እነርሱም ለእናትዬዋም ሆነ ለልጁ ሕይወት አስጊ ሊሆኑ የሚችሉበት ደረጃ አለ ። ከእነርሱም ውስጥ አንደኛው የልጁ አቀማመጥ ትክክለኛ አለመሆን ነው በዚህም ምክንያት በመውለድ ጊዜ ከፍተኛ ችግር እያጋጠማቸው የሞቱ እናቶች ቁጥር ጥቂት አይደለም።

ነፍሰ ጡር ሴቶች በተቻለ መጠን ከሚመጣው ችግር ለመጠበቅ ከእርግዝና ጊዜ ጀምሮ እስከሚወለድ ድረስ ለእነርሱ የሚደረገውን ምርመራ ቢከታተሉ መልካም ነው ።

ነገሩ አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት በጥናት እንደተደረሰው ከሚሞቱት



www.ethiopianorthodox.org

የእናቶች ቁጥር ውስጥ አብዛኛው በወሊድ ምክንያት በመሆኑ ነው ።

የልጁ አቀማመጥ ትክክለኛ ካልሆነ በእናትዬዋ በኩል የምጥ ጊዜ መራዘም ፤ ከውስጥ ልጁን የያዘው ማኅፀን መቀደድ ፤ ደም በብዛት መፍሰስ ሲሆኑ በልጁ ደግሞ በእትብቱ መታነቅወይም ትክክለኛ ባልሆነ አመጣጡ መታፈን ናቸው ። ይህ የማኅፀን መቀደድም ሆነ የደም በብዛት መፍሰስ ሴትዬዋን ያለ ጥርጥር ለሞት ያደርሳታል ። ምናልባት ቶሎ ርዳታ ካገኘች ልትተርፍ ትችላለች ። ልጁም ራሱን ችሎ በሳንባው አማካኝነት መተንፈስ የሚችለው ከተወለደ በኋላ ስለሆነ ከዚያ በፊት ግን የምግቡንም ይሁን የመተንፈሱንሥራ የሚያከናውነው በእትብቱ በኩል ከእናቱ በሚተላለፍለት በመሆኑ እትብቱ ሲጳጠር ልጁን በሚያንቅበት ጊዜ ወይም አንድ የሚጫነው ነገር ሲኖር ይህን ሥራውን ስለሚያቋርጥ ወይም ስለሚቀንስ ልጁን ለሞት ያደርሰዋል ።

እንግዲህ ይህን ሁኔታ በቅድሚያ ተረድቶ አስፈላጊውን ርዳታ ማድረግ የሚቻለው ሴትዬዋ ወደሐኪም ቤት ከሄደች ነው ፤ ካለበለዚያ ግን አንዳንድ ሰዎች እንደሚያደርጉት እናትዬዋ በብዙ ተሰቃይታ እነርሱም አቅማቸው የማይፈቅድላቸው ሲሆን ለሞት ከተቃረበች በኋላ ወደ ሐኪም መውሰዱ እምብዛም ጠቃሚ መስሎ አይታይም ። ሌላው ችግር ደግሞ የእንግዴ ልጅ በጊዜው አለመውጣት ነው ። ይህም ከፍተኛ የደም መፍሰስን ስለሚያስከትል ለሞት ምክንያት ይሆናል ። ይህ ሁሉ ችግር ሁልጊዜ ይሆናል ማለት ባይሆንም ችግር ከመጣ በኋላ ከመሯሯጥና ሴትዬዋንም ጉዳት ላይ ከማድረስ አስቀድሞ መጠንቀቁ ይበጃል ። የእናትዬዋም መሞት የሚጎዳው ጠቅላላ ቤተሰቡን መሆኑግልጽ ስለሆነ መተንተኑ አስፈላጊ አይደለም ። በሰላም ከተገላገለች በኋላም ችግሩን አለፈች ማለት አይቻልም ። ምክንያቱም ምናልባት ከውስጥ ትንሽ ነገር ቢቀር ወይም ንጽሕናዋን በደንብ ባትጠብቅ የማኅፀን አካባቢ እንደ ቁስል በመሆኑና ደም በመፍሰስም በማማጥም ኃይሏን ስላጣች በቀላሉ ለመበከልና ከላይ እንደተጠቀሰው ዓይነት ችግር ላይ ለመድረስ ጊዜ አይወስድም።

ስለዚህ ወላድ ሴቶች ይህን ያህል ችግር ሊያጋጥማቸው የሚችልና ብዙ ጥንቃቄ የሚያስፈልጋቸው መሆኑ ሊታወቅ ይገባል ። ከወለዱ በኋላም ደም ስለፈሰሳቸው ስለሚያጠቡም ተፈላጊው ምግብና በርከት ያለ ፈሳሽ ነገር ያስፈልጋቸዋል ። ደህና ምግብም እንኳ ባይገኝ እቤት ውስጥ የተገኘውን ቶሎ ቶሎ መስጠት ይገባል ። በዚህ አጋጣሚ ሴት ልጆችን ማስገረዝ በመውለድ ጊዜ ችግር ሊያስከትል በመቻሉ ትክክለኛ አድራጎት አለመሆኑን ልጠቁም እወዳለሁ ።

በተጨማሪም በቁጥር በርከት ያሉ ልጆች መውለድ በኢኮኖሚ ብቻ ሳይሆን እላይ በተጠቀሱት ችግሮች ከፍተኛ ሚና ስላለው ሊታሰብበት የሚገባ ነው ። በእርግጥ ስለዚህ ሁኔታ ሲወሳ ብዙዎችደስ እንደማይሰኙግልጽ ነው ። ይሁን እንጂ ከሚያመጣው ችግር የተነሳ ሊታመንበት የሚገባ ሳይሆን አይቀርም ። አንዲት ሴት ደጋግማ ከወለደች የሚመጣው ችግር ፤

፭ኛ/ የማኅፀኗ ግድግዳ ስለሚላላ ልጁን በደንብ ስለማይዘው ትክክለኛ ያልሆነ አቀማመጥና በመውለድጊዜም ትክክለኛ ያልሆነ አመጣጥ እንዲኖረው ያደርጋል ።

፮ኛ/ ደም በብዛት እንዲፈስ ምክንያት ይሆናል ብዙ ደም እንኳ እንደአጋጣሚ ሆኖ ባይፈስ ደጋግሞ በመውለድዋ ብቻ የደም ማነስ በሽታ ሊያመጣ ይችላል ።

፯ኛ/ የማኅፀኗ አፍ ስለሚላላ ውርጃን ያስከትላል ውርጃም ራሱን የቻለ ከፍተኛ ችግር በእናትዬዋ ላይ የሚያደርስ ነው ።

እንዲሁም የተወለዱትን ልጆች በደንብ ተንከባክቦ ለማሳደግ ስለሚያስቸግር ልጆች የወላጅ ፍቅር አጥተው ጤናማ ወይም ትክክለኛ ያልሆነ አእምሮ ይዘው እንዲያድጉ ምክንያት ይሆናል ። ይህም ብቻ ሳይሆን አሥር ተወልዶ አምስት የመሞትን ሁኔታ ያስከትላል ። አካለ ጎደሎ ልጅ የመውለድ አጋጣሚም የሚኖረው አብዛኛውን ጊዜ በእነኝህ እናቶች ላይ ነው ።

እንግዲህ በአጠቃላይ ሴቶች ይህ የተሰጣቸው የመውለድ ጸጋ ታላቅ ቢሆንም ካለመረዳትና ካለመጠንቀቅ የተነሳ ብዙ ችግር ስለሚያጋጥማቸው ሊደረግ የሚገባውን እንክብካቤ ቸል አለማለት ይመረጣል ።

ተማሪ ነርስ የሺሐረግ ሥርጋዌ



# ኢ.ኦ.ተ.ሐ.ደ

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፣ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፣ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት

ስልክ ቍ. 116616
የመል. ሣ. ቍ. 3137
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org